# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

## የምግብ ደህንነት እና ጥራት ቁጥጥር አፈጻጸምን፣በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ


**ማውጫ ........................................................................................................................................ I**

**የከዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ (EXECUTIVE SUMMERY).............................................................. III**

የምግብ ዓይነቶች ቃላት ትርጉም................................................................................................................ VI

**ክፍል አንድ........................................................................................................................................ 1**

መግቢያ ........................................................................................................................................1
የባለስልጣን መ/ቤቱ አመሰራረት፤ ........................................................................................................1
የባለሥልጣኑ ራዕይ፣ተልዕኮ፣ አላማ፣ ....................................................................................................2
የባለስልጣኑ ሥልጣንና ተግባር፡.............................................................................................................3
የባለሥልጣን መ/ቤቱ መዋቅርና የሰው ኃይል፡- .........................................................................................4
የባለስልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ፤ ..................................................................................................5
***=ቀደም ሲል ኤልሲ ተከፍቶ የነበረ በመሆኑ የተጠቀሙበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡..................................................5
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ (AUDIT ISSUE) ...............................................................................................6
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት፣.................................................................................................................6
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፤ .........................................................................................................................6
የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (SYSTEM DESCRIPTION...................................................................................7

**ክፍል ሁለት፣ ....................................................................................................................................10**

**ግኝቶች ..........................................................................................................................................10**

2.1. ለምግብ አምራቾች፤ ላኪዎች፤አስመጪዎችና አከፋፋዮች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥና የምግብ ምዝገባ ስርዓትን ተመለከተ፤- ......10
የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡-...................... 10
በሀገር ውስጥ የተመረተና ከውጭ ሀገር እንዲገባ የተደረገ ምግብን ለመሸጥ ወይም ለህብረተሰቡ ለማቅረብ የሚያስችል ፈቃድን በተመለከተ፤-............................................................................................................ 12
የምግብ ምዝገባ ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤-..................................................... 13
2.2.የምግብ ማምረቻዎች የመልካም አመራረት ሥርዓት ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ፡-..................................................13
በማንኛውም የምግብ ንግድ ድርጅት የድርጅቱን ሥምና አድራሻ የያዘ የውጭ ማስታወቂያ መኖሩን በተመለከተ፤- ............... 14
ማንኛውም ምግብ ጤናማ አጠባበቅ እየተደረገለት ስለመሆኑ፤ ........................................................................ 15
ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች የግል ንጽህናን በተመለከተ፣ ....................................................... 17
በባለሥልጣኑ የሚከናወን የኢንስፔክሽን ሥራን በተመለከተ፡-....................................................................... 19
የተሟላ የምግብ ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ መኖሩን በተመለከተ፤- ..................................................................... 20
2.3. የቅድመና የድህረ ገበያ ቁጥጥር (ኢንስፔክሽን) ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ፤...........................................21
በምግቦች ላይ የፊዝኮኬሚካል፣ የማይክሮባዮሎጂና የቶክሲኮሎጂ ምርምራ መደረጉን በተመለከተ................................ 21
ናሙናዎችን በመውሰድ ወይም በመቀበል ምርመራ መደረጉን በተመለከተ፡-.......................................................... 22
ማንኛውም ምግብ በምርቱ የመጀመሪያ ማሸጊያ ገላጭ ጽሁፍ ያለው መሆኑን በተመለከተ፤-.......................................... 25
የምግብ ጥሬዕቃዎችና የማሸጊያ ቁሳቁሶች ቁጥጥርና ፈቃድን በተመለከተ፡- .............................................................. 26
ለህብረተሰቡ እየቀረቡ የሚገኙ ምግቦች ትክክለኛ ና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸው በተመለከተ፡- ............................... 28
የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምግቦች ላይ ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ፤- ........................... 28
ምግብ ነክ መረጃዎች በአንድ ማዕከል የሚያዙበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ.............................. 31

የኢንስፔክሽንና የምግብ መልቀቂያ የፈቃድ አሰጣጥ ሥራን በተመለከተ፡- ............................................................ 32

ለክልል የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራ አስፈላጊውን ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፡- ......... 33

**ክፍል ሦስት ........................................................................................................................................35**

**መደምደሚያ........................................................................................................................................35**

**ክፍል አራት ........................................................................................................................................38**

**የማሻሻያ ሀሳብ፤- ..................................................................................................................................38**

**አባሪ አንድ፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት.......................................................................................................41**

**አባሪ 2፡ የባለሥልጣኑ ድርጅታዊ መዋቅር /ORGANAISATIONAL STRUCTURE OF FMHACA/ ...............................................45**

**አባሪ 3፡ በናሙና የታዩ የመንግሥትና የግል ተቋማት ..........................................................................................46**

**አባሪ 4፡ በባለስልጣን መ/ቤቱ ድህረ ኢንስፔክሽን ሳይደረግ ፈቃዳቸው የታደሰ ድርጅቶች ዝርዝር ..................................................47**

**አባሪ 5፡ የተከለሱ የአምራች ድርጅቶች ፋይል ዝርዝር (የቀረቡና ያልቀረቡ).......................................................................50**

**አባሪ 6፡ በድርጅቶች ሊሟሉ የሚገባቸው ሁኔታዎች ዝርዝር.........................................................................................52**

**አባሪ 7፡ በባለስልጣኑ ሬድ ኢንስፔክትድ ናቸው ተብለው በ 2010 እቅድ ተይዘው የነበሩ የተዘጉና አድራሻቸው የማይታወቅ ድርጅቶች .............53**

## የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ (Executive Summery)

ምግብ ለሰው ልጅ ጤና በመሰረታዊነት ከሚያስፈልጉት ነገሮች አንዱና ዋነኛው በመሆኑ በተገቢው ሁኔታ ጥራቱና ደህንነቱ ጠብቆ በማምረት ወደ ተጠቃሚው ካልደረሰ ጉዳት የማድረስ መጠኑም የዛኑ ያህል የከፋ ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ ከምግብ ደህንነት እና ጥራት ቁጥጥር ጋር በተያያዘ የሚከተሉት ዋና ዋና ግኝቶች ተመልክተዋል፡፡ እነርሱም፡-

- ፈቃድ ሳያወጡ እና ፍቃድ ሳያድሱ በምግብ ማምረት ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ እና መስፈርቱን ባለማሟላታቸው ከክልል ፈቃድ የተከለከሉ በፌዴራል ተቋሙ ፍቃድ እንዲያገኙ የተደረጉ ድርጅቶች መኖራቸው፤
- የህጻናት እና ተጨማሪ (መደበኛ አመጋገብን የንጥረ ምግብ ፍላጎት ለማሟላት የሚዘጋጅ ምግብ) ምዝገባ ውጭ በሌሎቹ ምግቦች ላይ የምግብ ምዝገባ እየተከናወነ አለመሆኑ፣
- ኤጀንሲው የምግብን ደህንነትና ጥራት ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑትን የምግብ ጥራት ምርመራ ላብራቶሪዎች በማደራጀት የተሟላ የምግብ ደህንነትና ጥራት ቁጥጥር የማያደርግ መሆኑ፤
- የናሙና አወሳሰድ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፡-
  - ✓ ናሙናዎቹን ወደ ላብራቶሪ እራሱ የምግብ አስመጪው እንዲወስድ የሚደረግ መሆኑ፤
  - ✓ ከጤና ኳራንቲን ጣቢያዎች የሚላከው ናሙና ውጤት የሚመጣው በቀጥታ ለላከው ጣቢያ ሳይሆን ለባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት መሆኑ እና የምርመራው ውጤት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ መፈቀዱ ከአስመጪዎቹ ፋይል ጋር እንዲያያዝ ወደ ጣቢያዎቹ/ኬላዎቹ የማይላክ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
  - ✓ የምርመራው ውጤት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ፈቃድ በሚሰጡ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች (ኳራቲን ጣቢያዎች) ተጠናቅሮ እንዲያዝ አለመደረጉ እና በናሙና የሚወሰደው የፐርሰንት መጠን አለመወሰኑ፣
  - ✓ እንዲሁም ባለሙያዎቹ የማያውቁዋቸው የምግብ አይነቶች በመኖራቸው ናሙና ለመውሰድ የሚቸገሩበት ሁኔታ መኖሩ፤

- ✓ የምግብ ጥራትን በሚመረምሩ በሀገሪቱ ያሉ የመንግሥትና የግል ላብራቶሪዎች የሚጠቀሙባቸው እስታንዳርዶች አገሪቱ በምትመራባቸው መሰረት ስለመሆናቸው በባለሥልጣን መ/ቤቱ ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣
- ✓ ለማሳያ፡- በማንጎ ጁስ ምርመራ በተደረገ ወቅት በኢትዮጵያ የማንጎ ጁስ ደረጃ (Ethiopian Standard for Mango juice- Specification) (ES 2856:2016 ምርመራ ዘዴ (Test method) ES ISO 6633 መሰረት ሊድ ከፍተኛ መጠን 0.05 max መሆኑን በደረጃ ሲያስቀምጥ ነገር ግን ብሌስ አግሪ ፉድ ላብራቶሪ ሰርቪስ ኃላ.የተ.የግ.ማ ሊድ ከፍተኛ መጠን 0.30 max በመጠቀሙ 0.20 ሊድ (ከሚፈቀደው 15 ከመቶ በላይ የሆነ) የሊድ መጠን ያለውን የማንጎ ጁስ ወደ ገበያ እንዲሰራጭ የፈቀደ መሆኑ፣
- ✓ ለግል መጠቀሚያ ተብለው የሚገቡ ምግቦች እስከ 100 ኪ.ግ እና ለፕሮጀክት መጠቀሚያ ተብለው የሚገቡ ምግቦች ላይ ምርመራ እንዲከናወንባቸው አለመደረጉና ሳይመረመሩ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ መደረጉ፣
- ✓ በኬላዎች ላይ ናሙና ለመውስድ የሚያስችል በቂ ማራገፊያና ማቆያ ቦታ አለመኖር፤
- ✓ በተደጋጋሚ ከውጭ ምግብ የሚያስገቡ አስመጪዎች ላይ እስከ ስድስት ወር ምርመራ የማይካሄድ (Sampling based on frequency)መሆኑ፤
- ✓ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተከለሱ፣ የተበላሹ፣ የተጭበረበሩ፣የተበከሉ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብለው በተጠረጠሩ ምግቦች ላይ የላብራቶሪ ምርመራ እንዲካሄድ ማድረግና ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስም በአገልግሎት ላይ እንዳይውሉ ታሽገው እንዲቆዩ የማይደረግ መሆኑ፤
- ✓ ባለሥልጣኑ የተከለሱ ወይም ከባዕድ ነገር ጋር የተቀላቀሉ ምግቦችን ለመለየት የሚያስችል ላብራቶሪ እንዲቋቋም አለማድረጉ፤
- ✓ ተበላሹ ተብለው የሚቀርቡ  አንድ አይነት የሆኑ ምግቦች ወደ ብሌስ ላብራቶሪ እና  የኢትዮጵያ የተሰማሚነት ምዘና ድርጅት ተልከው ውጤታቸው የተለያየ መሆኑን፤

- የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምግቦች እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ ተቆጥረውና ተመዝግበው እንደያዙ አለመደረጉ፣

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች መፍትሄ የማያገኙ ከሆነ ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀ ምግብ ለህብረተሰቡ ማቅረብ የማያስችል መሆኑን በኦዲቱ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የምግቦችን ደህንነትና ጥራት ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማትን የቁጥጥር ደረጃዎች አዘጋጅቶ ለምግብ አምራች ድርጅቶች፣ ለጥራት መቆጣጠሪያ ላብራቶሪዎች፣ ለአስመጪዎች፣ ለላኪዎች፣ ለአከማችና ለአከፋፋይ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፣ ማደስ፣ ማገድ እና መሰረዝ የሚያስችል የአሠራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- በሁሉም የምግብ አይነቶች ላይ ባለሥልጣኑ የምግብ ምዝገባ በማከናወን ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የምግብ ጥራት ምርመራ የናሙና ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ እና ላብራቶሪዎች በማደራጀት ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምግቦች እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ ተቆጥረውና ተመዝግበው እንዲሁም ከሌሎች ምግቦች ተለይተው ጥቅም ላይ እንደማይውሉ የሚገልጽ ጽሁፍ በመለጠፍ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቦታ እንዲከማቹ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ከላይ የተገለጹቱን ግኝቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች ባለሥልጣን መ/ቤቱ በዋነኛነት የተቋቋመበትን ዓላማና ኃላፊነት ለመወጣት ስለሚያግዘው በተጠቀሱት ችግሮች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ በማመቻቸት በአዋጁ እና በደንቡ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት ጉዳዩን በማሳወቅ፣ በመከታተልና በመቆጣጠር ኃላፊነቱን መወጣት ይጠበቅበታል፡፡

## የምግብ ዓይነቶች ቃላት ትርጉም

**ምግብ፤**ማለት ማንኛውም በጥሬነቱ፤በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የተዘጋጀ ለንግድ ወይም በሌላ መንገድ ለህብረተሰቡ አገልግሎት ቀርቦ ለሰው ምግብነት የሚውል ሲሆን እርሱም የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

**የጨቅላ ህፃናት ምግብ፤**ከእንስሳ ወይም ከእጽዋት የሚገኝ ወተት ወይም ወተት መሰል ውጤት ሆኖ አግባብ ባለው የጨቅላ ህፃናት ምግብ ደረጃ መሰረት በፋብሪካ የተዘጋጀና ከውልደት እስከ ስድስት ወር እድሜ ላሉ ጨቅላ ህፃናት የንጥረ ምግብ ፍላጎትን ለሚሟላት የተዘጋጀ ነው፡፡

**የታዳጊ ህፃናት ምግብ፤** ከእንስሳ ወይም አትክልት የሚገኝ ወተት ወይም ወተት መሰል ውጤት ሆኖ አግባብ ባለው የህፃናት ምግብ ደረጃ መሰረት በፋብሪካ የተዘጋጀ ከስድስት ወር እስከ ሶስት አመት የሆነን ህፃንን ለመመገብ ተስማሚ እንደሆነ የተገለጸ ወይም በሌላ መልኩ ገበያ ላይ የዋለ ነው፡፡

**ማሟያ ምግብ፤** የእናት ጡት ወተት፤የጨቅላ ህጻን ወይም የሕጻን ምግብ ለሕጻኑ የምግብ ፍላጎት በቂ ሳይሆን ሲቀር ለምግቦቹ ማሟያነት ተስማሚ ሆኖ በፋብሪካ የሚዘጋጅ ነው፡፡

**ተጨማሪ ምግብ፤**ማንኛውም መደበኛ አመጋገብን የንጥረ ምግብ ፍላጎት ለማሟላት የሚዘጋጅ የንጥረ ምግብ ወይም ፊዚዮሎጂካል ውጤት ያላቸው የቫይታሚን ወይም የማዕድን ወይም የሌሎች ንጥረ ነገሮች በነጠላ ወይም በጣምራ የሚገኙበትና በተወሰነ መጠን እንዲወሰድ ታስቦ በካፕሱል፣ በእንክብል፣ በዱቄት፣ በፈሳሽ፣ በጠብታ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ የሚዘጋጅነው፡፡

**ልውጥ ሕያው ምግብ፤** በዘረመል ምህንድስና የተለወጠ የስጋ ወይም ለምግብነት ሊውል የሚችል የእጽዋት ተዋጽኦ ነው፡፡

## ክፍል አንድ

### መግቢያ

1. በሀገራችን በዕቅድ የተቀመጡትን ማንኛውንም የልማት እና እድገት ግቦች ማሳካት የሚቻለው ህብረተሰቡ ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ ምግብ ሲመገብ፣ የሚኖርበት አካባቢ ከብክለት የጸዳ ሲሆን፣ በተለያየ ምክንያት ጤናው ሲታወክም ህክምና የሚያገኝባቸው ጤና ተቋማት ደረጃቸውን የጠበቁ ሲሆኑ እንዲሁም ሙያዊ ብቃትና ሥነ ምግባር ባለው ጤና ባለሙያ ሲታከም እና ከህመሙ ለመፈወስ የሚወስዳቸው መድኃኒቶችም ጥራት፣ደህንነት፣ ፈዋሽነትና አግባባዊ አጠቃቀም ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

2. ምግብ ለሰው ልጅ ጤና በመሰረታዊነት ከሚያስፈልጉት ነገሮች አንዱና ዋነኛው መሆኑ ይታወቃል፡፡ይሁን እንጂ በተገቢው ሁኔታ ጥራቱና ደህንነቱ ጠብቆ በማምረት ወደ ተጠቃሚው ካልደረሰ ጉዳት የማድረስ መጠኑም የዛኑ ያህል የከፋ ነው፡

3. ደህንነቱና ጥራቱ ባልተጠበቀ ምግብ ምክንያት በሕብረተሰቡ ጤና ላይ ሊደርስ የሚችለውን የጤና ችግር ለመከላከል፣ጥራት ያለው ምግብ ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት፣ለጤና ተስማሚ የሆነ ምግብ ማምረት፣ የተመረተውንም ምግብ በጥንቃቄ መያዝና ማከማቸት እንደዚሁም ማከፋፈል ያስፈልጋል ይህም ሲሆን በሀገራችን ለህብረተሰቡ እየቀረበ ያለውን ምግብ ደህንነትና ጥራት ለማረጋገጥ ይቻላል፡፡

4. በሀገራችን በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች በምግብ ወለድ በሽታዎች ህይወታቸውን ስለሚያጡ ይህንን ጉዳት ለመቀነስና ብሎም ለማጥፋት እንዲቻል የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 661/2002 እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም እንዲረዳ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 299/2006 እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

### የባለሥልጣን መ/ቤቱ አመሰራረት፤

5. በሀገራችን የህብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጠው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በስሩ የሚገኙ የተለያዩ ኤጀንሲዎችና የክልል ጤና ቢሮዎች ሲሆኑ የተለያዩ ሥራዎች በማከናወን ላይ ይገኛሉ፤ በጤናው ዘርፍ የተለያዩ አካላት ያሉ

ሲሆን ይህም የጤና አገልግሎት ሰጪ፣ የጤና ግብአቶች አቅራቢና የጤና ግብአትና አገልግሎት ተቆጣጣሪ ናቸው፡፡

6. ከነዚህ መካከል  የጤና ቁጥጥር ዘርፉን ስንመለከት ከዚህ በፊት በተለያዩ ቦታዎች ተበታትኖ ባልተቀናጀ መልኩ ሲሰራ የነበረ ሲሆን እነዚህም በዋናነት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ስር ሆነው ፤

7. መድኃኒትን በተመለከተ እስከ 1991 ዓ.ም በጤና ጥበቃ ሚ/ር ስር የመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር መምሪያ እንዲሁም፤የምግብና አካባቢ ጤና አገልግሎትን በተመለከተ እስከ 2001 ዓ.ም በጤና ጥበቃ ሚ/ር ውስጥ በሚገኘው የሀይጅን መምሪያ ሆኖ የተለያዩ የቁጥጥር ሥራዎች ሲሠሩ ነበር፡፡የጤና ተቋማትና ጤና ባለሙያዎች ምዝገባና ፈቃድ በተመለከተ እስከ 2001 ዓ.ም በጤና ጥበቃ ሚ/ር ውስጥ በነበረው የጤና ተቋማትና ጤና ባለሙያዎች ምዝገባና ፈቃድ መምሪያ ውስጥ ሲሠራ ነበር፡፡

8. የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ከተካሄደ በኋላ በጤና ዘርፍ ሰፍኖ የቆየውን የተበታተነና ጥራት የጎደለውን የአስተዳደርና የቁጥጥር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የጤናና ጤና ነክ ግብዓት አገልግሎቶች ጥራት ቁጥጥር በሚል የሥራ ሂደት እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ይህንን የቁጥጥር ሥራ በህግ አግባብ ለመደገፍ የሚያስችል የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 የወጣ ሲሆን፣ዘርፉን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የተለያዩ መመሪያዎችና ህጎች በማውጣት የተለያዩ የቁጥጥር ስራዎች በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

**የባለሥልጣኑ ራዕይ፣ተልዕኮ፣ አላማ፣**

**ራዕይ፡-**

ጥራት ያለው የጤና አገልግሎትና ግብዓት ለሁሉም ዜጎች መስጠት ነው፤

**ተልዕኮ፡-**

9. የምግብ፤የመድኃኒትና የጤና ተቋማት እንዲሁም የጤናና ባለሙያዎችን የብቃት ማረጋገጫ በመስጠትና በመቆጣጠር፤በምዝገባና በጥራት ምርመራ የግብዓቶች ጥራት፤ደህንንትና ፈዋሽነት በማረጋገጥ እንዲሁም አግባባዊ አጠቃቀምን ለማስፈን ወቅታዊ መረጃዎችን በማቅረብ የህብረተሰቡን ጤና ማበልጸግና መጠበቅ ነው፡፡

**ዓላማ፡-**

10. የምግብን ደህንነትና ጥራትን፤ የመድኃኒትን ደህንነት፤ፈዋሽነት፤ጥራትና አግባባዊ አጠቃቀምን፤የጤና፤ የህክምናና የመድኃኒት ባለሙያዎችን ሙያዊና የሥነ-ምግባር ብቃትን፤የጤና ተቋማትን ድርጅታዊ ብቃትን፤የሀይጂንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ ለግልና ለህብረተሰብ ጤና ተስማሚ መሆኑን፤በማረጋገጥ የተጠቃሚውን ጤንነት መጠበቅ ነው፤

**የባለስልጣኑ ሥልጣንና ተግባር፡**

11. በአዋጅ ቁጥር 661/2002 መሰረት ባለሥልጣኑ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባሮች መካከል ፡-

- የምግቦችን ደህንነትና ጥራት፣ የመድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነት፣ ጥራትና አግባባዊ አጠቃቀም የሕክምና ባለሙያዎችን ብቃትና አሠራር፣የሀይጅንና የአካባቢ ጤናን እና የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማትን የቁጥጥር ደረጃዎች አዘጋጅቶ አግባብ ላለው አካል ያቀርባል፣ ሲጸድቁም በተግባር ላይ መዋላቸውንና መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
- ለልዩ የጤና ተቋማት፣ ለምግብ ወይም ለመድኃኒት አምራች ድርጅቶች፣ ለጥራት መቆጣጠሪያ ላቦራቶሪዎች፣ ለባዮኢኩቫለንስ ማእከላት፣ ለአስመጪዎች፣ ለላኪዎች፣ ለአከማችና ለአከፋፋይ ድርጅቶች እና ለክልል ተሻጋሪ የጤና አገልግሎት ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤
- የምግብ፣የመድኃኒት፣የጤና ባለሙያዎችና የጤና ተቋማት ጥራትና ብቃት የሚጠናከርበትንና የሚስፋፋበትን የፖሊሲ ሀሳብ ያመነጫል፣ ረቂቅ ሕጎችን ያዘጋጃል፣ለመንግሥት ውሳኔም ያቀርባል፤
- የምግብ፣የመድኃኒት፣የአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣የጤና ባለሙያዎች እና የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማትን በሚመለከት የመረጃዎች ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤
- በምግብ ወይም በመድኃኒት መመረዝ ወይም መበከል ምክንያት ለሚደርስ የሞት፣ የጤንነት መታወክ መንስኤ የሆነውን ንጥረ ነገር ልዩ ልዩ ናሙናዎችን በመውሰድ ወይም በመቀበል መርምሮ ምንነታቸውን ያረጋግጣል፣ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤
- ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የጥራት ምርመራ ላቦራቶሪዎችን ያደራጃል፤

- ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ ምግቦች፣ መድኃኒቶች፣ ጥሬ ዕቃዎች፣ የማሸጊያ ቁሳቁሶችና የአስክሬን ቁጥጥር ያካሂዳል፣ የመግቢያና የሙውጫ ፍቃዶች ይሰጣል፤
- የምግቦችን ደህንነት፣ ጥራት እና የመድኃኒቶችን ደህንነታቸው፣ ፈዋሽነታቸውና ጥራታቸውን ገበያ ላይ ከዋሉ በኋላ ለማረጋገጥ የድህረ ገበያ ቅኝት በማካሄድ ተገቢውን የቁጥጥር ሥራ ያካሂዳል አስፈላጊውን እርምጃም ይወስዳል፤
- የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ምግቦች፣ መድኃኒቶችና ጥሬ ዕቃዎቻቸው በአግባቡ መወገዳቸውን ያረጋግጣል፤
- ከተለያዩ ተቋማት የሚወጡ ክልል ተሻጋሪ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በሕዝብ ጤና ላይ ጉዳት የማያስከትል መሆኑን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤
- ሕገወጥ ምግቦችን፣ መድኃኒቶችና የጤና አገልግሎቶችን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ እርምጃዎችንም ይወስዳል፤
- ከአንድ ክልል በላይ ለህብረተሰቡ ለመጠጥ የሚቀርብ ውኃ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤
- በፌዴራል መንግሥት ስር ያሉ ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማት ተገቢውን የሐይጅንና አካባቢ ጤና አገልግሎት መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤
- በፌዴራልና በክልል ያለው የቁጥጥር ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሆን ለማድረግ ለክልል የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡

የሚሉት ይገኙበታል፡፡

**የባለሥልጣን መ/ቤቱ መዋቅርና የሰው ኃይል፡-**

**ድርጅታዊ መዋቅር፡-**

12. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአንድ ዋና ዳይሬክተርና በሶስት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚመራ ሆኖ በ25 ዳይሬክቶሬቶች የተደራጀ ሲሆን በተጨማሪም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ሰባት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና የዓለም አቀፍ ኤርፖርቶች ቁጥጥርን ጨምሮ 17 የሚሆኑ የመግቢያና የመውጫ ኬላዎች አሉት፡፡(አባሪ 2 ተያይዟል)

**የሰው ኃይል፤**

13. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በታሕሣሥ ወር 2010 ዓ.ም 216 ሴት ሠራተኞች፣ 365 ወንድ ሠራተኞች በድምሩ 581 የቋሚ ሰራተኞች አሉት፡፡ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያለው የቋሚ ሠራተኞች የሰው ኃይል በሙያ ሲተነተን ማስተርስ 40 (7%) የመጀመሪያ ዲግሪ 284 (49%) ዲፕሎማ 92 (16%) ከ9-12ኛ ክፍል 77 (13%)እና ከ1-8ኛ ክፍል 65(11%) ቲቪቲ 23 (4%) ነው፡፡

**የባለሥልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ፤**

14. የኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግሥት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2007-2009 ዓ.ም ድረስ የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጭ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | የተፈቀደ በጀት | | ድምር | ስራ ላይ የዋለ በጀት | | ስራ ላይ የዋለ በጀት በመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መደበኛ | ካፒታል | | መደበኛ | ካፒታል | መደበኛ | ካፒታል |
| 2007 | 60,854,746.40 | 4,486,220.44 | 65,340,966.84 | 50,792,284.39 | 4,185,601.86 | 83% | 93 % |
| 2008 | 88,203,170.00 | 10,763,110.00 | 98,966,280.00 | 77,194,296.24 | 32,878,579.27 | 87% | 305 %*** |
| 2009 | 106,517,200 | 10,404,860.00 | 116,922,060.00 | 9,132,809,017.40 | 7,704,849.02 | 86% | 74% |

*****=ቀደም ሲል ኤልሲ ተከፍቶ የነበረ በመሆኑ የተጠቀሙበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡**

**የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ፤**

15. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የምግብ ደህንነትና ጥራት ቁጥጥር አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ በምግብ ደህንነትና ጥራት ሥራዎች ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ችግሮች ወይም ክፍተቶች እና መንስዔያቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡

**የኦዲት አካባቢ (audit area)**

16. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ Audit Area) **የምግብ ደህንነትና ጥራት ቁጥጥር አፈጻጸም፣ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ**

በሆነ መንገድ እየተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡

**የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ (audit issue)**

17. በተለየው የኦዲት አካባቢ (audit area) ስር ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል እነሱም፡-

1. ለምግብ አምራቾች፣ላኪዎች፣አስመጪዎችና አከፋፋዮች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥና የምግብ ምዝገባ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤
2. በምግብ ማምረቻዎች የመልካም አመራረት ሥርዓት ቁጥጥር መደረጉን ማረጋገጥ፤
3. የምግብ አምራች አስመጪ ላኪና ጅምላ አከፋፋዮች የምግብ የቅድመና የድህረ ገበያ ቁጥጥር(ኢንስፔክሽን) ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣

የሚሉት ናቸው፡፡

**የኦዲት መመዘኛ መስፈርት፣**

18. በኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን ሶስት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) ለመገምገም የሚያስችል 46 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ተዘጋጅተው ባለሥልጣን መ/ቤቱ አስተያየት እንዲሰጥበት ተልኮ አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቱ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

**የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፤**

19. የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2009 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው የሦስት በጀት ዓመታትን ከ2007- 2009 ዓ.ም እና የ2010 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

20. የኦዲት ቡድኑ የባለሥልጣን መ/ቤቱን አሠራር የሚመለከቱ የተለያዩ አዋጆች፣ ሠነዶች ማስረጃዎችን፤የመሰረታዊ የሥራሂደት ለውጥ የጥናት ሪፖርት፣ የየአመቱን ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፣ የስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የሥራ

አመራር (የማኔጅመንት)ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ ባለሥልጣን መ/ቤቱን በሚመለከት የወጡ የተለያዩ ብሮሸሮች መጽሔቶችና የተለያዩ መመሪያዎችን የከለሰ ሲሆን፤

21. በባለሥልጣን መ/ቤቱ እና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቃሊቲ መግቢያና መውጫ ጤና ኳራንቲን ጣቢያ፣ በኤርፖርት ካርጎ መግቢያና መውጫ ኬላ፣ በቦሌ ኤርፖርት ተርሚናል መግቢያና መውጫ ኬላ፣ በሞጆ ጤና ኳራንቲን ጣቢያ፣ በአዳማ ጤና ኳራንቲን ጣቢያ፣በምግብ ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ (ፓስተር) የመስክ ምልከታ በማድረግ ለሥራ ኃላፊዎችም መጠይቅ አቅርቧል፡፡

22. በተጨማሪም በናሙና በተመረጡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን፤በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ፤በኦሮሚያ ጤና ቢሮ፤በብሌስ አግሪ ፉድስ ላብራቶሪ፤በተለያዩ የፓስታ፤የብስኩት፤የወተት፤የዘይት፤የጨውና የውኃ ማምረቻዎች በመገኘት የመስክ ጉብኝት በማድረግና ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች መጠይቅ በማቅረብና የተለያዩ ሰነዶችን በመከለስ እና አሠራሩን በአካል ተገኝቶ በመገምገም የተከናወነ ሲሆን የታዩት ተቋማት ዝርዝር በአባሪ 5 ተይዟል፡፡

**የአሰራር ሥርዓት መግለጫ** (System description

23. <u>**የምግብ ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት የአሠራር ሥርዓት መግለጫ**</u>

- በደንበኞች አገልግሎት የቅድመ ግምገማ ማጣራት ተካሂዶባቸው ተቀባይነት ያገኙትን የአዲስ ምዝገባ፤የምዝገባ ለውጥ እና የዳግም ምዝገባ ማመልከቻዎችን ሰነዶችን ተቀብሎ በቅደም ተከተላቸው በዳታ ቤዝ መዝግቦ መያዝ፤
- የሚመዘገቡ ምግቦች ሰነዶችን በመገምገም ጥራትና ደህንነታቸውን ማረጋገጥ የገበያ ፈቃድ መስጠት ፤
- የእድሳት ጊዜ ሲደርስ የእድሳት መስፈርት ላሟሉ ምግቦች እድሳት ማካሄድ፤
- በተመዘገቡ ምግቦች ላይ የሚደረጉ የምዝገባ ለውጦችን ገምግሞ መስፈርት ያሟሉትን ማጽደቅ፤
- ገበያ ላይ እንዲውሉ በተደረጉት ምግቦች ላይ የደህንነት ክትትል (ቪጅላንስ) ማካሄድ፤

- ❖ በድህረ ገበያ የደህንነት ክትትል ውጤት መሰረት ወይም በተጠቃሚዎች የደህንነት ችግር እንዳለባቸው ቅሬታ ቀርቦ በተረጋገጠባቸው ምግቦች ላይ የገበያ ፈቃድ እገዳና ስረዛ ማካሄድ፤

24. **<u>የምግብ ጤናና ጤና ነክ ተቋማት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት</u>**

- ❖ በደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የቀድመ ማጣራት ተካሂዶባቸው ተቀባይነት ያገኙትን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማመልከቻዎችን ተቀብሎ በቅድም ተከተላቸው ባዳታ ቤዝ መዝግቦ መያዝ፤
- ❖ የምግብ አምራቾች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ሚሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ የቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን በማካሄድ መስፈርቱን የሚያሟሉ ከሆነ ፈቃድ እንዲሰጣቸው መረጃውን በደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ስር ወደሚገኘው የምግብ አምራች፤ አስመጪና ጅምላ አከፋፋዮች ፈቃድ ቡድን መላክ፤
- ❖ ድርጅቶቹ የሚያመርቷቸው እና የሚያሰራጩዋቸው ምግቦች ጥራታቸውና ደህንነታቸው የጠበቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የመልካም አመራረት አሰራር ሂደታቸው እና የድህረ ገበያ ቁጥጥር ማካሄድ፤
- ❖ ከህብረተሰቡና ሌሎች አካላት የሚመጡ ጥቆማዎች በማጣራት ተገቢውን እርምጃ መውሰድ፤
- ❖ የቁጥጥር ህጎች ተከትለው በማይሰሩ አምራች ድርጅቶች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ፤
- ❖ በአምራች ድርጅቶች ውስጥ በተለያየ ምክንያት ጥቅም ላይ የማይውሉ ምግቦች ሲኖሩ በአግባቡ መወገዳቸውን ማረጋገጥ፤
- ❖ ለቅ/ጽ/ቤቶችና የክልል ተቆጣጣሪ ደጋፍ ማድረግ፤

25. **<u>የምግብ ጥራት ምርመራ ዳይሬክቶሬት</u>**

- ❖ ነባርና አዲስ የሚዘጋጁ የምግብ የፊዚኮኬሚካል ጥራት መመርመሪያ ዘዴዎችን በትክክል መስራታቸውን የተለያዩ አድቫንስ አናሊቲካል ዘዴዎችን በመጠቀም ማረጋገጥ፤
- ❖ አዳዲስ የምግብ የፊዚኮኬሚካል ጥራት መመርመሪያ ዘዴዎች አንድ ወጥ የሥራ መመሪያ ማዘጋጀት(መከለስ)፤
- ❖ በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር ሚገቡ ምግቦችን ጥራት ለማረጋገጥ የፊዚኮኬሚካል ምርመራዎችን ማከናወን፤

- በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምግቦችን ጥራት ለማረጋገጥ የማይክሮናዮሎጂ ምርመራዎችን ማከናወን፤
- በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምግቦችን ጥራት ለማረጋገጥ የቶክሲኮሎጂ ምርመራዎችን ማከናወን፤

26. **ማዕከላዊ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

- የምግብና መድኃኒት አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት፤
- የድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ማካሄድና የህግ ጥሰት ፈጽመው በሚገኙ ተቋማት አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ፤
- የድህረ ገበያ ኢንስፔክሽንና ቅኝት ሥራዎች ማካሄድ፤
- ህገ ወጥ የምግብ ንግድ ቤቶች ቁጥጥር ማካሄድ፤
- መለስተኛ የምግብና መድኃኒት ላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ማካሄድ፤
- አስፈላጊውን የቁጥጥር መረጃ ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤

**ክፍል ሁለት፣**

**ግኝቶች**

**2.1. ለምግብ አምራቾች፤ ላኪዎች፤አስመጪዎችና አከፋፋዮች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥና የምግብ ምዝገባ ስርዓትን ተመለከተ፤-**

**የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡-**

27. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ለምግብ አምራች ድርጅቶች፣ ለጥራት መቆጣጠሪያ ላቦራቶሪዎች፣ለአስመጪዎች፣ለላኪዎች፣ ለአከማችና ለአከፋፋይ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፣ ማደስ፣ ማገድ እና መሰረዝ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

28. ባለሥልጣኑ ድርጅቶቹ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከወሰዱ በኋላ ክትትል በማድረግ ፈቃዱ መታደሱ እንዲረጋገጥና ፈቃድ ባለማሳደሳቸው እንዲጠየቁ በማድረግ መታገድ ያለበት እንዲታገድና ፈቃዱም መሰረዝ ካለበት እንዲሰረዝ የሚያደርግበት ሥርዓት የዘረጋ ቢሆንም ተግባራዊ እንዲሆን አለመደረጉን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

29. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ የምግብ አምራቾች፤ ላኪዎች፤ አስመጪዎችና አከፋፋዮች ፋይል፤

- በናሙና ተመርጠው ከቀረቡት ፋይሎች ውስጥ የድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ሳይከናወን ከ2008 እስከ 2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ለ37 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲታደስ መደረጉ፤
- ከባለስልጣኑም ሆነ ክክልል ከሚመለከታቸው አካላት ፈቃድ ሳይኖራቸው ምግብ የሚያመርቱና የጥራት መቆጣጠር ላብራቶሪ ሥራ የሚሠሩ ድርጅቶች መኖራቸው፣ (ዘርዝሩ በአባሪ 8 ተያይዟል)
- ለባለሥልጣኑ የምግብ ማምረት ፈቃድ የመለሱ ድርጅቶችን ሥራ ላይ እንዳሉ በማድረግ የኢንስፔክሽን እቅድ ውስጥ እንዲካተቱ መደረጉ፤
- በባለሥልጣኑ በ2010 ዓ.ም ኢንስፔክሽን ይደረግባቸዋል ተብለው ቀይ፣ ቢጫ እና አረንጓዴ ተብለው የተለዩ ድርጅቶች ውስጥ ጥብቅ ክትትል እየተደረገባቸው ነው ተብለው በእቅድ ከተያዙ ድርጅቶች ሁለቱ (2) ዘግተው ፈቃድ የመለሱ መሆኑ፣

- ድርጅቶቹ መስፈርት ባለማሟላታቸው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን ፈቃድ የተከለከሉ የምግብ አምራች ድርጅቶች ከፌዴራል ባለሥልጣን መ/ቤቱ ፈቃድ እንዲያገኙ መደረጉ፣ (ዝርዝሩ በአባሪ 7 ተያይዟል፡፡)

30. ከባለሥልጣኑም ሆነ ከክልሎች ፈቃድ ሳያወጡ በሚሠሩ የምግብ አምራቾች እና ድርጅቶች መልካም የአመራረት ሥርዓትን ባለመከተላቸው (Good Management Practice) ስለተሰረዘ ፈቃድ ወይም ስለተወሰደ እርምጃ የሚያሳይ ማስረጃ በባለሥልጣኑ ማቅረብ አለመቻሉ በኦዲቱ ወቅት ከቀረበ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

31. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች የብቃት ማረጋገጫ ሳያወጡ የሚያመርቱ በጥቆማ ሲገኙ የሚታገዱ፣ የመልካም አመራረት ችግር ከታየባቸው ዕርምጃ የሚወስዱ፣እንደ ችግሩ አንገብጋቢነት ሁኔታ እገዳ የወጣባቸው የአምራቾች እና የአስመጭዎች መረጃዎች ያሉዋቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡እንዲሁም ኢንስፔክሽን ሳያደርጉ የብቃት ማረጋገጫ ስለተሰጣቸው እና ፈቃድ ሳይኖራቸው የምግብ ጥራት ላብራቶሪ ስለሚሰሩ ድርጅቶች ኤጀንሲው በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ ምላሽ አልሰጠም፡፡

32. አስፈላጊው ቁጥጥር በመግቢያና መውጫ ኬላዎች እየተደረገ የሚገኝ ሲሆን ነገር ግን የመግቢያና የመውጫ ኬላ ባልተቋቋመበት የሀገሪቱ ክፍል በሕገወጥ የሚገቡ በመኖራቸውና እስካሁን ምንም አይነት ፈቃድ ሳይኖራቸውና በባለሥልጣኑ ያልተደረሰባቸው አምራቾች በመኖራቸው ምክንያት በተለይም ለሥራ እድል ፈጠራ ተብሎ የጤና ማረጋገጫ ሳያገኙ ለማምረት ተደራጅተው የሚሰሩ እንዳሉ ለአብነት ያህል የኦቾሎኒ፣ ከረሜላ ማምረቻዎች …..፡፡በድንበር አካባቢ ያለው ቁጥጥር በመግቢያና መውጫ ኬላዎች ድንበር በተለያዩ ቦታዎች ላይ ክፍት በመሆኑ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንን ኬላ ተከትለን የምንሰራ በመሆኑ ከኛ ቁጥጥር ውጪ በሆነ ሁኔታ የሚገቡ ምግቦች መኖራቸውን እና ሌሎች አካላት ስለጉዳዩ ትኩረት መስጠት ያለባቸው መሆኑን፣ ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት አስተያየት፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርት በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

33. ኃላፊዎቹ ይህንን ምላሽ ቢሰጡም ባለሥልጣን መ/ቤቱ ጥቆማ ካልደረሰው በስተቀር ቁጥጥር ያላደረገ በመሆኑ እና አለ የተባለውም መረጃ ኦዲቱ

እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ባለመቅረቡ በምላሹ የተጠቀሰው እርምጃው ስለመወሰዱ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

34. ምግብን ማምረትም ሆነ ከውጭ ማስገባት እና ማከፋፈልን በተመለከተ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ ህግ ወጥ የሆነና ንጽህናው ያልተጠበቀ ምግብ ባልተፈቀደ ቦታና ማምረቻ በሰፊው እየተመረተ ወደ ገበያ በመግባት ለህብረተሰቡ በብዛት እንዲከፋፈልና ጥቅም ላይ እንዲውል በመደረጉ የሀገርን ኢኮኖሚ ከመጉዳቱም በላይ መተኪያ የሌለውን የሰው ልጅ ጤና ለችግር እንዲጋለጥ ያደርጋል፡፡

## በሀገር ውሰጥ የተመረተና ከውጭ ሀገር እንዲገባ የተደረገ ምግብን ለመሸጥ ወይም ለህብረተሰቡ ለማቅረብ የሚያስችል ፈቃድን በተመለከተ፤-

35. ማንኛውም ምግብ ሲመረት፣ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ፣ ወደ ውጭ ሲላክ፣ ሲዘጋጅ፣ ሲከማች፣ ሲከፋፈል፣ ሲጓጓዝ፣ ሲሸጥ ወይም ለህብረተሰቡ ሲቀርብ ባለስልጣን መ/ቤቱ እንዲያውቀውና ፈቃድ እንዲያገኝ ሊደረግ ይገባል፡፡

36. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በመቆጣጠሪያ ኬላና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት ከሚደረግ ኢንስፔክሽን ውጪ ምግብ ሲጓጓዝ እንዲሁም ገበያ ላይ የዋሉ ምግቦችን ደህንነት እና ጥራት የማይረጋገጥ፣ የድህረ ገበያ ቅኝት በማድረግ እና የቁጥጥር ሥራ በማካሄድ አስፈላጊው እርምጃ የማይወሰድ መሆኑን በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና የመስክ ምልከታ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 4 ቀርቧል

37. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት ምላሽ የድህረ ገበያ ቅኝት በየሱፐር ማርኬት በሚውሉ ምርቶች ላይ የሚደረግ መሆኑን እና ችግር ያለበት ከተገኘ ጥቅም ላይ እንዳይውልና አምራቹ የማስተካከያ ዕርምጃ እንዲወሰድ የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

38. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ መመሪያው ላይ እንደተቀመጠው የድህረ ገበያ ቅኝት ቁጥጥር በሁሉም ንግድ ድርጅቶች ላይ እንጂ በሱፐር ማርኬት ላይ ብቻ የሚወሰን ባለመሆኑ እንዲሁም ድህረ ገበያ ቅኝት ስለማድረጋቸው እና እርምጃ ስለመውሰዳቸው የሚያሳይ ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

39. ምግቦች በአግባቡ እና በጥንቃቄ ተይዘው ቁጥጥር ተደርጎባቸው ለተጠቃሚው እንዲደርሱ ካልተደረጉ ለብልሽት የሚዳረጉ በመሆናቸው በህብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡

**የምግብ ምዝገባ ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤-**

40. ከውጭ አገር ለሚገባም ሆነ በአገር ውስጥ ለሚመረት ማንኛውም ምግብ፣ የምግብ ምዝገባ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

41. ይሁን እንጂ በአገር ውስጥ ለሚመረትና ከውጭ አገር ለሚገባ ማንኛውም ምግብ የምግብ ምዝገባ ስርዓት (ምግቦቹ የተመረቱበት እና የአመራረት ሂደታቸው ምን እንደሚመስል ታይቶ የሚመዘገብበት ስርዓት) የተዘረጋ ቢሆንም የህጻናት እና ተጨማሪ (መደበኛ አመጋገብን የንጥረ ምግብ ፍላጎት ለማሟላት የሚዘጋጅ ምግብ) ምዝገባ ብቻ የሚያከናውን ሲሆን በሌሎቹ ምግቦች ላይ የምግብ ምዝገባው እየተከናወነ አለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

42. ይህንን በሚመለከት የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ተጠይቀው መመሪያ ተዘጋጅቶ የፀደቀ ስለሆነ ሁሉንም ምግቦች ለመመዝገብ ስራው መጀመሩን ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

43. ኃላፊው ይህንን ምላሽ ቢሰጡም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀ ድረስ ከህጻናት እና ተጨማሪ (መደበኛ አመጋገብን የንጥረ ምግብ ፍላጎት ለማሟላት ከሚዘጋጅ ምግብ) በስተቀር ሌሎች ምግቦች ለመመዝገባቸው ማስረጃ ያልቀረበ ስለሆነ ምዝገባው ስለመከናወኑ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

44. ይህ አሠራር ያልተመዘገቡ፣ ደህንነትና ጥራታቸው ያልተጠበቀ ምግቦች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው እንዲሁም አገር ውስጥ ተመርተው እንዲሰራጩና ለምግብነት እንዲውሉ መንገድ ይከፍታል፡፡

**2.2.የምግብ ማምረቻዎች የመልካም አመራረት ሥርዓት ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ፡-**

**በማንኛውም የምግብ ንግድ ድርጅት የድርጅቱን ሥምና አድራሻ የያዘ የውጭ ማስታወቂያ መኖሩን በተመለከተ፤-**

45. ማንኛውም ከባለሥልጣኑ ፈቃድ የወሰደ የምግብ ንግድ ድርጅት የድርጅቱን ሥምና አድራሻ የያዘ የውጭ ማስታወቂያ ቢያንስ በአማርኛ ቋንቋ ጽፎ ድርጅቱ በሚገኝበት ቦታ የለጠፈ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

46. ይሁን እንጂ በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩት የምግብ ንግድ ድርጅቶች ውስጥ

- ስምንቱ የውጭ ማስታወቂያ የሌላቸውና አድራሻቸው የማይታወቅ፤
- ስድስቱ አድራሻቸው ታውቆ የውጭ ማስታወቂያ የሌላቸው መሆናቸው፣
- የድርጅታቸውን ሥምና አድራሻ የያዘ የውጭ ማስታወቂያ በግልጽ የማይታይ እና ቀለማቸው የለቀቁ እንዳሉ እና
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ማስታወቂያውን ያልለጠፉ ድርጅቶች እንዲለጥፉ አለማድረጉን፤
- በተለይ በናሙና ተመርጠው የታዩ ሁሉም የምግብ አስመጪ ድርጅቶች ሥምና አድራሻ የያዘ የውጭ ማስታወቂያ ድርጅቱ በሚገኝበት ቦታ ባለመለጠፉ ምክንያት ኦዲቱን ለማከናወን አድራሻቸውን ለማግኘት ሲባል እስከ ቀበሌ ጽ/ቤት ድረስ በመሄድ ለማግኘት ሙከራ ቢደረግም በባለሥልጣኑ በተመዘገበ አድራሻቸው ያልተገኙ መኖራቸው፣

በኦዲቱ ወቅት ከቀረበ መጠይቅ በመስክ ጉብኝት እና ከተከለሰ ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ (ዝርዝሩ አባሪ 7 ተያይዟል)

47. የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ለነባራዊ ሁኔታ በሰጡት አስተያየት ሁሉም ድርጅቶች የውጭ አቅጣጫ ጠቋሚ ማስታወቂያ እንዲያዘጋጅ እየተሰራ ነው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፤ ኃላፊው ይህንን ቢገልጹም የኦዲት ቡድኑ በተዘዋወረባቸው ቦታዎች የውጭ ማስታወቂያ የሌላቸውን ተቋማት ለማየት የቻለ በመሆኑ ምክንያቱን እንዳለ ለመቀበል ያቸግራል፡፡

48. የአድራሻ ጠቋሚ ማስታወቂያ ባለመኖሩ ምክንያት ህጋዊ የሆኑ አምራቾችና አከፋፋዮችን ለመለየት የማይቻል በመሆኑ ህገ ወጥ የሆኑትን በመከታተል እርምጃ እንዳይወሰድና ህጋዊ የሆኑትን እንዳይበረታቱ እንዲሁም ህጋዊ ሆነው የሚሰሩትንም በወሰዱት ፈቃድ መሰረት የአከመቻቸት እና የአጓጓዝ ሥርዓቱን እየተገበሩ መሆኑን ለመከታተል እና የዕርምት እርምጃ ለመውሰድ እንዳይቻል ከማድረጉም በላይ የምግብ ምርትን ሽያጭ በመደበቅ መንግሥት ማግኘት ያለበትን ግብር እንዳይሰበስብ ያደርጋል፡፡

## ማንኛውም ምግብ ጤናማ አጠባበቅ እየተደረገለት ስለመሆኑ፤

49. ማንኛውም የምግብ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን ወይም የተቀበለውን መስፈርት ተከትሎ ለማንኛውም ምግብ ጤናማ አጠባበቅ በማድረግ ቶሎ ሊበላሽ የሚችል ምግብን በሚያከማችበት፣ ለዕይታ በሚያቀርብበት፣ በሚያሽግበት ወይም በሚያጓጉዝበት ጊዜ ምግቡ በተገቢው የሙቀት መጠን እንዲቀመጥ እና እንዲጓጓዝ እየተደረገ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

50. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው በታዩ የምግብ ማምረቻ ድርጅቶች

- በናሙና ተመርጠው በታዩ ድርጅቶች በቀዝቃዛ ስፍራ መቀመጥ እና መጓጓዝ የሚገባው ምርት በቀዝቃዛ ስፍራ ተቀምጦ እንዲጓጓዝ እና ወደ ገበያ ሲቀርብም እንደየ ባህሪው በጥንቃቄ እንዲያዝ አለመደረጉን፣
- ቶሎ ሊበላሽ የሚችል ምግብ  በተገቢው የሙቀት መጠን ወይም የቅዝቃዜ ሁኔታ ተጠብቆ እየተጓጓዘና እየተከማቸ አለመሆኑ፣



**ፎቶ ቁጥር 1 ፡ማቀዝቀዣ የሌላቸው የወተት እና በሸራ የተሸፈነ የውሃ ማጓጓዣዎች**

- የምግብ አምራች፣ አስመጪና አከፋፋይ የሆኑ ድርጅቶች ማንኛውንም ምግብ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሰረት ጤናማ በሆነ መንገድ ለማምረትና ለመጠበቅ የሚያስችል የክምችት ሥርዓት መመሪያ አለመኖር፣

- በምግብ ማምረቻዎች አከባቢ የእሳት ማጥፊያ፣ ምግቡን ማከማቻ ቦታ፣ የሠራተኞች የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና መስጫ ክሊኒክ፣ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር፣ አየር ማዘዋወሪያ (ኤሲ)፣ ጽዳት መጠበቂያ ላውንደሪ፣ የድንገተኛ አደጋ መውጫ በር ወ.ዘ.ተ) የሌላቸው ድርጅቶች መኖራቸውን፣ እና

- ምግቦች በክምችትም ሆነ ለሽያጭ በሚቀርቡበት ጊዜ በፀሀያማ ቦታ የሚቀመጡበት ሁኔታ መኖሩ፣

- የምግብ ማከማቻዎቹ ንጽህና የሌላቸው፣ በተገቢው የሙቀት መጠን ወይም የቅዝቃዜ ሰንሰለት ያለው የተሟላ የምግብ ማጓጓዣ የሌላቸው መሆኑ፣

- ከውጭ የሚገቡ ምግቦች የክምችት እና የማጓጓዝ ሂደት ላይ ባለሥልጣኑ ቁጥጥር የማያደርግ መሆኑን

በኦዲቱ ወቅት ተመርጠው በታዩ የምግብ አቅራቢ እና አከፋፋይ ድርጅቶች በተደረገ የመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡ (**ዝርዝር ማስረጃው በአባሪ 6 ተያይዟል፡፡**)

51. የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህንን በተመለከተ ተጠይቀው በድህረ ኢንስፔክሽን ወቅት የሚደረጉ የኢንስፔክሽን ምርቶች፣ ቼክ ሊስቶች ያሉ መሆኑን፣

ክሊኒክ በተመለከተ “Outsource” በማድረግ ውል ፈጽመው ስለሚገኙ እና የሠራተኞች የሥራ ላይ የደህንነት የጤና ምርመራ በቼክ ሊስቱ መካተቱን ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

52. ኃላፊዎቹ ይህንን ምላሽ ቢሰጡም የቼክ ሊስቱ መኖር ብቻ የተመለከቱት ግዴታዎች በአግባቡ ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋገጥ የማያስችል መሆኑ እና ደጋፊ ማስረጃም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረቡ እንዲሁም በመስክ ጉብኝት ወቅት የተጠቀሱት ክፍተቶች መኖራቸው ስለተረጋገጠ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

53. ደረጃውን የጠበቀ ጤናማ አጠባበቅ ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ የምግብ ማምረቻና ማከማቻ በሌለበት ሁኔታ ምግብን ማምረት፣ ማከማቸት እና መሸጥ የምግቡን ጥራት ከመቀነሱ በላይ ምግቡ ጥቅም የሚሰጥ እንዳይሆንና ሊይዘው የሚገባውን የምግብ ይዘት እንዲቀይርና ተጠቃሚዎችን በሽታ ላይ እንዲወድቁ ያደርጋል፡፡



ፎቶ ቁጥር 2፡- የተሟላ የመጀመሪያ ደረጃ ክሊኒክ እና የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር የሌላቸው የምግብ ማምረቻዎች በከፊል

## ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች የግል ንጽህናን በተመለከተ፣

54. እንደሥራው ባህሪ ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች የግል ንጽህናቸው እንዲጠበቅ በማድረግ በሥራ ወቅት የምግብን ጥራትና ደህንነት

መጠበቂያ አልባሳት ሊጠቀሙ ይገባል፡፡ ድርጅቶቹም መስፈርቱን አሟልተው ሠራተኞቻቸው እንዲሰሩ የሚያደርጉ ስለመሆኑ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

55. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች የግል ንጽህናቸው እንዲጠበቅ በማድረግ በሥራ ወቅት የምግቡን ጥራትና ደህንነት መጠበቂያ አልባሳት የሚጠቀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ክትትልና ቁጥጥር አያደርግም፡፡ በናሙና በታዩ እና በምርት ላይ ከነበሩ ከሶስቱ ሁለቱ የምግብ አምራች ድርጅቶች የምግብን ጥራትና ደህንነት መጠበቂያ አልባሳት እንደማይጠቀሙ እንዲሁም ምግቦችን ጓንት ሳይጠቀሙ በእጃቸው ወደ ማሽጊያዎች እንደሚያስገቡ፣ በናሙና የታዩ ሁሉም የምግብ አምራች ድርጅቶች በመመሪያው ላይ በተቀመጠው መሰረት የግል ንጽህናቸውን ለመጠበቅ የሚያስችል በቂ የልብስ ማጠቢያ ቦታ፣ የምግብ መመገቢያ ቦታ፣ በቂ የመጸዳጃ ቤትና የገላ መታጠቢያ ቦታ ያልተሟላ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡



**ፎቶ ቁጥር 3፡- የምግብን ጥራትና ደህንነት መጠበቂያ አልባሳት ሳይጠቀሙ የጨው ምርት በማምረት ሥራ ላይ**

56. ይህንን በተመለከተ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ በቼክ ሊስት ተካቶ እየተሰራበት ነው፡፡የምግብ ደህንነት ለማስጠበቅ የሠራተኞች ጤና ምርመራ፣ አልባሣት እና ንጽህናን በተመለከተ ቁጥጥር ይደረጋል በማለት አስተያየት የሰጡ ቢሆንም በተደጋጋሚ ለመግለጽ እንደተሞከረው ግዴታዎቹ በመመሪያና በቼክ ሊስት ላይ የሰፈሩ ስለሆነ ብቻ ተግባራዊ ተደርጓል ማለት

ስለማይቻል የተሰጠው አስተያየት በማስረጃ የተደገፈ ስላልሆነ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

57. ምግብ ለምርት የሚሆን ግብአትን ከማከማቸት አንስቶ የማምረት ሂደቱ ተጠናቆ ለተጠቃሚው እስከሚደርስ ድረስ ባለው ሂደት ሁሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ስለሚያፈልግ ሠራተኞች ተገቢውን መሳሪዎች በመጠቀም ሊያመርቱ ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ሠራተኞቹን ለአደጋ፣ ምግቡን ለብክለት እና ተመጋቢውንም ለጤና ጉዳት እንዲጋለጥ ያደርጋል፡፡

## በባለሥልጣኑ የሚከናወን የኢንስፔክሽን ሥራን በተመለከተ፡-

58. ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ የኢንስፔክሽን ሥራ የምግብ ፈቃድ በሰጣቸው ድርጅቶች ላይ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በማንኛውም የምግብ ማምረቻ ድርጅት በሚደረግ ኢንስፔክሽን ወቅት የሚገኙ ማንኛውም ክፍተቶች በኢንስፔክሽን ቼክ ሊስት ተሞልተው የግምገማ ነጥባቸው ከድርጅቶቹ ፋይል ጋር ሊያያዝና የግምገማው ነጥብ ኮፒው ለድርጅቶቹ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ድርጅቶቹም በተሰጣቸው አስተያየት መሰረት የዕርምት እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

59. ይሁን እንጂ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ በወሰዱ በአምራች፣ አስመጪ፣ አከፋፋይና አጓጓዥ ድርጅቶች በባለሥልጣኑ በሚደረግ ኢንስፔክሽን ወቅት፡-

- የሚገኙ ማንኛውም ክፍተቶች በኢንስፔክሽን ቼክ ሊስት ተሞልተው የግምገማ ነጥባቸው በባለሥልጣኑ ከፋይላቸው ጋር የማይያያዝ መሆኑ፤
- የግምገማው ነጥብ ኮፒው ለድርጅቶቹ እንዲሰጥ የማይደረግ መሆኑ፤
- በኢንስፔክሽን ወቅት የተገኘው ክፍተት ድርጅቶቹ የገቡትን ግዴታ በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ማስተካከያ ስለማድረጋቸው በባለሥልጣን መ/ቤቱ ክትትል በማድረግ የማይረጋገጥ መሆኑን

በኦዲቱ ወቅት በናሙና ለታዩ አምራች ድርጅቶች ከቀረበ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ (አባሪ 3 ሦስት) ተያይዟል፡፡

60. ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው የግምገማ ቼክ ሊስቱ ከፋይላቸው ጋር መያያዙን፣ የተሰጣቸው አስተያየት (Comment) ለድርጅቱ ኮፒ ተደርጐ የሚሰጥ መሆኑን እና ስለማስተካከሉም በድጋሚ በማንኛውም ሠዓት ቁጥጥር እንደሚደረግ ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

ኃላፊዎቹ ይህ እንደሚከናወን ምላሽ ቢሰጡም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀ ድረስ ማስረጃ ያልቀረበ ስለሆነ እንዲሁም በናሙና ለታዩ አምራች ድርጅቶች ከቀረበ መጠይቅና ከተከለሱ ማስረጃዎች ይህ እንደማይደረግ በመረጋገጡ የተሰጠውን ምክንያት ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

61. ድርጅቶቹ ጉድለታቸውን አውቀው ማስተካከል የሚገባቸውን ክፍተት መተማመኛ ከባለስልጣን መ/ቤቱ ጋር ተፈራርመው ጊዜ ገደብ ተደርጎ ክፍተቱን እንዲያስተካካሉ ካልተደረገ ችግሩ እንዳይስተካከል እና እንዲባባስ በማድረግ ምግቡ ደህንነቱና ጥራቱ የተጓደለ እንዲሆን የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ ያደርጋል፡፡

**የተሟላ የምግብ ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ መኖሩን በተመለከተ፤-**

62. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የምግብ ጥራት ምርመራ ላብራቶሪዎች ሊያደራጅና ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡

63. ይሁን እንጂ፡-

- የምግብን ደህንነትና ጥራት ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑትን የምግብ ጥራት ምርመራ ላብራቶሪዎች በማደራጀት የተሟላ የምግብ ደህንነትና ጥራት ቁጥጥር የማያደርግ መሆኑ፤
- በናሙና ተመርጠው በታዩ አዳማ ኳራንቲን ጣቢያ፤ ሞጆ ኳራንቲን ጣቢያ፤ቃሊቲ ኳራንቲን ጣቢያ እንዲሁም በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ የኤርፖርት ተርሚናል እና የአዲስ አበባ ኤርፖርት ካርጎ መግቢያና መውጫ ኬላ የምርመራ ላብራቶሪዎች አለመኖር፤
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሚቆጣጠረው የምግብ ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ (ፓስተር) ላብራቶሪው አስፈላጊ በሆኑ መሳሪያዎችና ግብአቶች ያልተደራጀና ደረጃውን የጠበቀና ሁሉንም መስፈርት (Parameter) ለመስራት የሚያስችል ላብራቶሪ አለመሆኑ፤
- የምግብ የጥራት ምርመራ በፓስተር የሚደረገው በሁለት ምግቦች ላይ ማለትም በጨውና ዘይት ላይ ብቻ መሆኑ በሀገር ውስጥ የምግብ አምራቾችም በማምረቻ ተቋማቸው ውስጥ የተሟላ ላብራቶሪ የሌላቸው እና ሙሉ በሙሉ ላብራቶሪም ክፍል ያላደራጁ አምራቾች መኖራቸው፤
- በየኬላዎች የሚገኙ ኢንስፔክተሮች በእይታ (physical & organoleptic inspection) ለሚያደርጉዋቸው ምርመራ የሚያግዙ የተሟላ መሳሪያ (Sampling tools) የሌላቸው መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ ቦታዎች በተደረገ የመስክ ምልከታ፣ ከቀረበ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

64. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ላብራቶሪ የማይሰሩ ቴስቶችን ከውጭ ላብራቶሪዎች (outsource) በማድረግ እንዲሰራ እየተደረገ መሆኑን፣ በአብዛኛው ደህንነታቸውና ጥራታቸው ጥርጣሬ የሚያሳድሩ የምግብ አይነቶች ቀጥታ ወደ ላብራቶሪ የሚላኩ መሆኑንና ዘመናዊ የሩዝ ናሙና መውሰጃ መሣሪያ በግዢ ላይ መሆኑን ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

65. ባለሥልጣኑ የሚጠቀምበት ላብራቶሪ በተገቢው እንዲደራጅ አለመደረጉና ከተወሰኑ ቦታዎች በስተቀር በሌሎች የባለስልጣኑ መቆጣጠሪያ ቦታዎች የጥራት ማረጋገጫ መሣሪያዎች አለመኖር በአገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ምግቦች ደህንነትና ጥራት ትክክለኛነት ሙሉ ለሙሉ እንዲረጋገጥ ስለማያደርግ ጥራቱን ያልጠበቀ ምግብ ለህብረተሰቡ እንዲቀርብና እንዲመገበው በማድረግ መተኪያ የሌለው የሰው ልጅ ህይወት ችግር ላይ እንዲወድቅ ያደርጋል፡፡

### 2.3. የቅድመና የድህረ ገበያ ቁጥጥር (ኢንስፔክሽን) ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ፤

### በምግቦች ላይ የፊዝኮኬሚካል፣ የማይክሮባዮሎጂና የቶክሲኮሎጂ ምርምራ መደረጉን በተመለከተ

66. ባለሥልጣኑ በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምግቦችን ጥራት ለማረጋገጥ የፊዝኮኬሚካል፣ የማይክሮባዮሎጂና የቶክሲኮሎጂ ምርምራ ሊያደርግ ይገባል፡፡

67. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ እንደተቻለው፡-

- በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምግቦችን ጥራት ለማረጋገጥ በሁሉም ምግቦች ላይ እንደምግቡ አይነት የፊዝኮኬሚካል፤ የማይክሮባዮሎጂና የቶክሲኮሎጂ ምርምራ ሊደረግ ሲገባ 18(አስራ ስምንት) የምግብ አይነቶች ብቻ ተለይተው ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ውጭ በሚገኝ በግል ድርጅት ላብራቶሪ የምግብ ጥራት ምርመራ የሚደረግ መሆኑ፤
- የምግብ ላብራቶሪ ምርመራ የሚያከናውነው ብሌስ አግሪ ፉድ ላብራቶሪ የተባለ የግል ተቋም የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት ወይም ከራሱ

ከባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ስለመሆኑ ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አለማቅረቡ፣

- ባለሥልጣኑ በኦሮሚያ ክልል ለሚገኘው ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ በስሩ ከሚያስተዳድረው ሰበታ ኢንዱስትሪያል ኮምፕሌክስ የጁስ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ የማንጎ ጁስ ናሙና ተወስዶ በብሌስ አግሪ ፉድ ላብራቶሪ የፊዚኮኬሚካል እና የማይክሮባዮሎጂ የተከናወነው ፍተሻ ውጤት ለውስጥ መረጃ ብቻ እንዲጠቀሙበትና ላብራቶሪው በኢትዮጵያ ውስጥ በማንጎ ጁስ ፍተሻ አክርዲቴሽን የምግብ ጥራት ማረጋገጫ ተግባር ለማከናወን ፈቃድ የሌለው እና በተቋሙ የተከናወነው ምርመራ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ በቀን መስከረም 12/2009 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 02/12/32/545 የገለጸ መሆኑ፣ በተቃራኒው ግን ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከጨውና ከምግብ ዘይት በስተቀር ከውጭ የሚገቡ ምግቦችን የማንጎ ጁሶችን ጨምሮ በዚሁ ላብራቶሪ እንዲመረመሩ በውስጥ ማስታወሻ ቁጥር ም/ጥ/ም/ዳ 093/08 በቀን 14/08/08 ዓ.ም ለማዕከላዊ ቅ/ጽ/ቤት ያሳወቀ መሆኑ፣
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የምግብ ላቦራቶሪ ምርመራ የሚያከናውነውን የግል ተቋም የምግብ ምርመራ እንዲያከናውን የመረጠበት መስፈርት እና የተገባ ውል የሚያሳይ ማስረጃ ኦዲቱ እሰከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ በባለሥልጣኑ ያልቀረበ መሆኑ፣

68. ስለ ሁኔታው የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ምላሽ አልሰጡም፡፡

69. ባለሥልጣኑ በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምግቦችን ጥራት ለማረጋገጥ የፊዝኮኬሚካል፣ የማይክሮባዮሎጂና የቶክሲኮሎጂ ምርምራ አለማድረጉ የምግብ ጥራት እንዳይጠበቅ በማድረግ የሰው ጤንነት ላይ ጉዳት ያደርሳል፡፡

## ናሙናዎችን በመውሰድ ወይም በመቀበል ምርመራ መደረጉን በተመለከተ፡-

70. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ምግቦችን ናሙናዎች በመውሰድ ወይም በመቀበል ምርመራ በማድረግ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

71. ይሁን እንጂ የምርመራው ናሙና አወሳሰድ በስርዓት የማይመራ መሆኑ፣

✓ ናሙናዎቹን ወደ ላቦራቶሪ እራሱ የምግብ አስመጪው እንዲወስድ የሚደረግ መሆኑ፣

- ✓ ከጤና ኳራንቲን ጣቢያዎች የሚላከው ናሙና ውጤት የሚመጣው በቀጥታ ለላከው ጣቢያ ሳይሆን ለባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት መሆኑ እና የምርመራው ውጤት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ መፈቀዱ ከአስመጪዎቹ ፋይል ጋር እንዲያያዝ ወደ ጣቢያዎቹ/ኬላዎቹ የማይላክ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- ✓ የምርመራው ውጤት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ፈቃድ በሚሰጡ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች (ኳራቲን ጣቢያዎች) ተጠናቅሮ እንዲያዝ አለመደረጉ እና በናሙና የሚወሰደው የፐርሰንት መጠን አለመወሰኑ፣
- ✓ እንዲሁም ባለሙያዎቹ የማያውቋቸው የምግብ አይነቶች በመኖራቸው ናሙና ለመውሰድ የሚቸገሩበት ሁኔታ መኖሩ፤
- ✓ የምግብ ጥራትን በሚመረምሩ በሀገሪቱ ያሉ የመንግሥትና የግል ላብራቶሪዎች የሚጠቀሙባቸውን እስታንዳርዶች አገሪቱ በምትመራባቸው መሰረት ስለመሆናቸው በባለሥልጣን መ/ቤቱ ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣

  ለማሳያ፡- በማንጎ ጁስ ምርመራ በተደረገ ወቅት በኢትዮጵያ የማጎ ጁስ ደረጃ (Ethiopian Standard for Mango juice- Specification) (ES 2856:2016 በ ምርመራ ዘዴ (Test method) ES ISO 6633 መሰረት ሊድ ከፍተኛ መጠን 0.05 max መሆኑን ደረጃ ሲያስቀምጥ ነገር ግን ብሌስ አግሪ ፉድ ላብራቶሪ ሰርቪስ ኃላ.የተ.የግ.ማ ሊድ ከፍተኛ መጠን 0.30 max በመጠቀሙ 0.20 ሊድ (ከሚፈቀደው 15 ከመቶ በላይ የሆነ) የሊድ መጠን ያለውን የማንጎ ጁስ ወደ ገበያ እንዲሰራጭ የፈቀደ መሆኑ፣
- ✓ ለግል መጠቀሚያ ተብለው የሚገቡ ምግቦች እስከ 100 ኪ.ግ እና ለፕሮጀክት መጠቀሚያ ተብለው የሚገቡ ምግቦች ላይ ምርመራ እንዲከናወንባቸው አለመደረጉና ሳይመረመሩ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ መደረጉ፣
- ✓ በኬላዎች ላይ ናሙና ለመውሰድ የሚያስችል በቂ ማራገፊያና ማቆያ ቦታ አለመኖር፤
- ✓ በተደጋጋሚ ከውጭ ምግብ የሚያስገቡ አስመጪዎች ላይ እስከ ስድስት ወር ምርመራ የማይካሄድ መሆኑ፤(Sampling based on frequency)መሆኑ፤
- ✓ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተከለሱ፣ የተበላሹ፣ የተጭበረበሩ፣የተበከሉ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብለው በተጠረጠሩ ምግቦች ላይ የላብራቶሪ ምርመራ እንዲካሄድ ማድረግና ውጤቱ

እስኪታወቅ ድረስም በአገልግሎት ላይ እንዳይውሉ ታሽገው እንዲቆዩ የማይደረግ መሆኑ፤

- ✓ ባለስልጣኑ የተከለሱ ወይም ከባእድ ነገር ጋር የተቀላቀሉ ምግቦችን ለመለየት የሚያስችል ላብራቶሪ እንዲቋቋም አለማድረጉ፤
- ✓ ተበላሹ ተብለው የሚቀርቡ አንድ አይነት የሆኑ ምግቦች ወደ ብሌስ ላብራቶሪ እና የኢትዮጵያ የተሰማሚነት ምዘና ድርጅት ተልከው ውጤታቸው የተለያየ መሆኑን፤

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ቅ/ጽ/ቤቶች እና የክልል ባለሥልጣን መ/ቤቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

72. የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ናሙና አወሳሰዳቸው የቀድሞ የምርመራ ውጤትን ማዕከል ያደረገ መሆኑ፣ የተጠረጠሩ ናሙናዎች ደግሞ በማንኛውም ጊዜ ወደ ላብራቶሪ የሚላኩ፣ መሆናቸውን፣ ናሙናዎቹን ወደ ላቦራቶሪ እራሱ የምግብ አስመጪው እንዲወስድ የሚደረግ መሆኑ የሚለው ልክ ሲሆን ነገር ግን ናሙናውን ወደ ላቦራቶሪ መላክ ወይም መወሰድ ያለበት በባለሙያው ቢሆንም ካለው የትራንስፖርት ችግር አንጻር ደረጃውን በጠበቀ ናሙና አስተሻሸግ በማሸግ እስከዋናው መ/ቤት ድረስ በአስመጪው እንዲመጣ በማድረግ ከዋናው መ/ቤት ወደ ላቦራቶሪው በባለሥልጣኑ ባለሙያ የሚሄድ መሆኑንና ላቦራቶሪዎች የሚጠቀሙባቸው ስታንዳርዶችን በተመለከተ በተለያዩ የሀገር ውስጥ ላቦራቶሪዎች የተለያየ ሪፖርት በመደረጉ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በራሱ ወጪ በውጭ ሀገር ደረጃውን የጠበቀ ላቦራቶሪ በማፈላለግ ምርመራው መከናወኑን፤ ናሙና ለመውሰድ በቂ ማራገፊያና ማቆያ ቦታን በተመለከተ ኬላዎችን የሚያስተዳድረው ገቢዎችና ጉምሩክ እንዲሁም የደረቅ ወደቦችን መሰረተ ልማት የሚያሟላው የኢትዮጵያ ባህርና ተራንዚት ወደቦቹ ለፍተሻና ናሙና ለመውሰድ ምቹ አለመሆናቸው ባለሥልጣን መ/ቤቱ በተደጋጋሚ የሚያሳውቅ መሆኑና ደረቅ ወደቦች ላይ የሚገነቡ ህንጻዎች የእኛን መስፈርት እንዲያሟሉ ተደርገው ስለማይገነቡ የተፈጠረ ችግር መሆኑን ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርት በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

73. የምግብ ናሙናው በተገቢው መልኩ አለመከናወኑ ህብረተሰቡ የማያውቃቸው ምግቦች እና ጥራቱን ያልጠበቀ ምግብ ለተጠቃሚው እንዲሰራጭ በማድረግ ጉዳት ያደርሳል፡፡

**ማንኛውም ምግብ በምርቱ የመጀመሪያ ማሸጊያ ገላጭ ጽሁፍ ያለው መሆኑን በተመለከተ፤-**

74. ማንኛውም ምግብ በምርቱ የመጀመሪያ ማሸጊያ (Primary Packing) ላይ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የተፃፈ ሆኖ በግልጽ የሚነበብና በቀላሉ የማይለቅ የምግቡን ይዘት ብቻ የሚገልጽ ጽሁፍ ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

75. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ እንደተቻለው በምርቱ የመጀመሪያ ማሸጊያ (Primary Packing) ላይ ገላጭ ጽሁፋቸው በደንብ የማይታይና የማይነበብ፣ ከሁለቱ ቋንቋ ውጭ በሌላ ቋንቋ የተጻፈባቸው፣ የምግቡን ይዘት የማይገልጹ፣ ከምግቡ ይዘት በተጨማሪ መጠቀስ የማይገባው ማስታወቂያ መሰል ሌላ ማብራሪያ የተጻፈባቸዉ ምግቦች በገበያ ላይ መኖራቸው በኦዲቱ ታውቋል፡፡




**ፎቶ ቁጥር 4፡- የምግቡን ያዘት የማይገልጽ እና ከምግቡ ይዘት በተጨማሪ መጠቀስ የማይገባው ማስታወቂያ መሰል ሌላ ማብራሪያ የተጻፈባት ማሸጊያ**




ፎቶ ቁጥር 5፡- በአማርኛ ወይም በእንግሊዘኛ የምግብ ይዘታቸው ያልተገለጸ ምግቦች

76. የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ በሰጡት አስተያየት ተመርተው ከመውጣታቸው በፊት ማሸጊያዎች ላይ የሚፃፉ ፅሁፎች ቁጥጥርና የድህረ ገበያ ቅኝት በማድረግ ማስተካከያ እንዲያደርጉ ማድረጋቸውንና እርምጃ መውሰዳቸውን የገለጹ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀ ድረስ ቁጥጥር ስለመደረጉና እርምጃ ስለመወሰዱ ማስረጃ ያልቀረበ ስለሆነ የሠጡትን አስተያየት ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

77. ማንኛውም ምግብ በምርቱ የመጀመሪያ ማሸጊያ (Primary Packing) ላይ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የተፃፈ ሆኖ በግልጽ የሚነበብና በቀላሉ የማይለቅ የምግቡን ይዘት ብቻ የሚገልጽ አለመሆኑ ተጠቃሚው የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈ ወይንም የተቃረበ፤ ከምን እንደተዘጋጀ የማይታወቅ፤የመሳሰሉት ችግሮች የሚገኙባቸው ምግቦች ለተጠቃሚው በማቅረብ የህዝብን ጤና አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል፡፡

## የምግብ ጥሬዕቃዎችና የማሸጊያ ቁሳቁሶች ቁጥጥርና ፈቃድን በተመለከተ፡-

78. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ የምግብ ጥሬዕቃዎችና የማሸጊያ ቁሳቁሶች ላይ ቁጥጥር በማካሄድ የመግቢያና የሙውጫ ፈቃድ የሚሰጥበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

79. ይሁን እንጂ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ እና በሀገር ውስጥ በሚመረቱ የምግብ ጥሬ ዕቃዎችና የማሸጊያ ቁሳቁሶች ላይ ቁጥጥር ለማካሄድና ፈቃድ ለመስጠት

የሚያስችል ስርአት ያልተዘረጋ መሆኑ፣አስመጪዎችና አምራቾች እንደ ግብዓት የሚጠቀሙበትን ጥሬ እቃ እና የማሸጊያ ቁሳቁስ ለማስገባት ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ተጨማሪ ፈቃድ የማይጠይቁ መሆኑ፣ማሸጊያዎቹ አንዴ ታትመው ለረጅም ጊዜ በማከማቻ የሚቆዩ በመሆኑ ምግቡ እንደተመረተ ማሸጊያዎቹ ጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረጉ፣ የምግብ ማሸጊያዎቹ የምግቡን ጥራት ከማስጠበቅ አኳያ የተዘጋጁ ስለመሆኑ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ቁጥጥር እና ክትትል በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ የማይወስድ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ የምግብ ማምረቻዎች በተደረገ የመስክ ምልከታ፣ከቀረበ መጠይቅና ማስረጃ በመከለስ ለማወቅ ተችሏል፡፡



**ፎቶ ቁጥር 6፡- አንዴ ታትመው ለረጅም ጊዜ በማከማቻ የሚቆዩ የምግብ ማሸጊያዎች በከፊል**

80. የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በመግቢያና መውጫ ላይ ምግብ ሆነ የምግብ ጥሬ ዕቃና የማሸጊያ ቁሳቁሶች በመመሪያው መሠረት ቁጥጥር የሚደረግባቸው መሆኑን ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት ላይ ገልጸዋል፡፣ ኃላፊዎቹ ይህንን የገለጹ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀ ድረስ ቁጥጥር ስለማድረጋቸው ማስረጃ አላቀረቡም፡፡

81. የማሸጊያ ቁሶቹ የተመረተ ምግብን ትክክለኛ ይዘት ማሳየታቸው ሥልጣን በተሰጠው አካል ተገቢው ቁጥጥር ካልተደረገባቸው የምግቡ ይዘት በየጊዜው በመቀያየር ማሸጊው ላይ የሚገለጸው እና ምግቡ ውስጥ የሚገኘው ይዘት የተለያየ እንዲሆን በማድረግ ህብረተሰቡን ለማሳሳት በር እንዲከፍት ያደርጋል፡፡

## ለህብረተሰቡ እየቀረቡ የሚገኙ ምግቦች ትክክለኛ ና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸው መለየታቸውን በተመለከተ፡-

82. በማቋቋሚያ አዋጁ መሰረት በሀገር ደረጃ በህጋዊ መንገድ ለህብረተሰቡ እየቀረቡ ለሚገኙት ምግቦች የምግብ ዝርዝር በማደራጀት በገበያ ላይ ያሉ ምግቦች ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ ህጋዊና ህገወጥ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ምግቦች እንዲለዩ ሊደረግ ይገባል፡፡

83. ይሁን እንጂ በሀገር ደረጃ በአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር ተመርተው በህጋዊ መንገድ ለህብረተሰቡ እየቀረቡ የሚገኙ ምግቦችን ለመቆጣጠር ባለሥልጣን መ/ቤቱ

- የምግብ ዝርዝር በማደራጀት በገበያ ላይ ያሉ ህጋዊና ህገወጥ ምግቦችን በመለየት ህብረተሰቡ እንዲያውቃቸው አለማድረጉ፤
- የምግብ ንግድ ማስታወቂያ በመገናኛ ብዙሀን ወይም በማናቸውም መንገድ ሲተላለፍ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መመሪያ መሰረት መሆኑ እንዲረጋገጥ አለመደረጉን

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በተደረገ ቃለ መጠይቅ ታውቋል፡፡

84. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው ቁጥጥሩን ለማጠናከር የምግብ ምርቶች እንዲመዘገቡ እየተደረገ መሆኑን ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ኃላፊዎቹ ይህንን ቢገልጹም ኦዲቱ እሰከተጠናቀቀ ድረስ ህጋዊና ህገ ወጥ ምግቦች ምዝገባን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ አስተያየቱን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

85. ደረጃቸውን ያልጠበቁ ምግቦች ላይ ተገቢው ቁጥጥር አለመደረጉ እና በሀገር ደረጃ ህብረተሰቡ ለምግብነት ሰለሚቀርቡለት ምግብ ጥራትና ደህንነት ግንዛቤ እንዲኖረው ባለመደረጉ በገበያ ላይ የሚያገኛቸውን ማንኛውንም ምግብ በመጠቀም ቋሚ የሆነ የጤና መታወክና አልፎም እሰከ ህይወት ማጣት የሚያደርስ የከፋ ጉዳት እንዲደርስ በር ይከፍታል፡፡

## የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምግቦች ላይ ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ፤-

86. ባለስልጣን መ/ቤቱ የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምግቦች እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ ተቆጥረውና ተመዝግበው፣ ከሌሎች ምግቦች ተለይተው

ጥቅም ላይ እንደማይውሉ የሚገልጽ ጽሁፍ በመለጠፍ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቦታ እንዲከማቹ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ፣ የአገልግሎት ጊዜው ያበቃ ምግብና ጥሬ ዕቃ  ደህንነቱና ጥራቱ ያልተጠበቀ መሆኑን ካተረጋገጠ አግባብ ባለው መንገድ እንዲወገድ ወይም ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፡፡

87. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው በታዩ የመቆጣጠሪያ ኬላዎች እና የሀገር ውስጥ የምግብ ማምረቻዎች፡-

- እያንዳንዱ የምግብ ምርት ዓይነትና መጋዘን ላይ የምርቱን ዓይነት፣ ምርቱ ያለበትን ሁኔታ (አያያዝ፣ አቀማመጥና የቆይታ ጊዜው ያለበትን ደረጃ) እና ሌሎች ስለምግቡ የሚገልጹ መረጃዎች በየጊዜው ስለመለጠፋቸው ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፣
- የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምግቦች እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ ተቆጥረውና ተመዝግበው እንዲሁም ከሌሎች ምግቦች ተለይተው ጥቅም ላይ እንደማይውሉ የሚገልጽ ጽሁፍ በመለጠፍ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቦታ እንዲከማች አለመደረጉ እና ለዚህም ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፣
- ከደረጃ በታች በመሆናቸው የሚወገዱ ምግቦች ጥቅም ላይ ከሚውሉ ምግቦች ጋር በአንድ መጋዘን ውስጥ ተደባልቀው እንዲቀመጡ መደረጉ በመስክ ምልከታ ወቅት መታወቁ፣
- የሚወገዱ የምግብ ምርቶች ተለይተው በአግባቡ ባለመያዛቸው በሰው ጤና ላይ ጉዳት በሚያደርስ መልኩ የሚያዙበት ሁኔታ መኖሩ፣ እንዲሁም
- የጥራት ችግር ያለባቸው እና በመጋዘን እንዲቀመጡ የተደረጉ ምግቦች ተመዝግበው እንዲቀመጡ በማድረግ የተመዘገቡት ምግቦች በሙሉ ስለመወገዳቸው የማይረጋገጥ መሆኑ፣
- የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ምግቦችና ጥሬ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ እና ከውጭ አገር የገባ ምግብ ደህንነቱና ጥራቱ ያልተጠበቀ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ አግባብ ባለው መንገድ መወገዱን ወይም ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ መደረጉን በባለሥልጣኑ የሚረጋግጥበት ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ እንዲሆን አለመደረጉ፣

- በሀገር ውስጥ ለሚወገድ ምግብ የባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ተቆጣጣሪዎች በተገኙበት በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አዋጅና ደንብ መሠረት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች በተውጣጣ ኮሚቴ አማካይነት አካባቢያዊ ተጽዕኖ በማያሳድር መልኩ እንዲወገድ ለማድረግ ባለስልጣኑ የተያዘው (የጥራት ጉድለት አለበት የተባለው) በሙሉ ስለመወገዱ የማያረጋግጥ እና ቃለ ጉባኤውን አጠናቅሮ የማይዝ መሆኑ፣
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ምግብን ለማሰወገድ ጥያቄ ሲቀርብ አንድ ተወካይ ከመላክ ውጭ ምግቡ ስለሚወገድበትና በሰው ጤንነት ላይ ስለሚያስከተለው ጉዳት የማያረጋግጥ መሆኑ፤
- ከሁለት ዓመት በላይ ተቀምጠው በሰው ጤና ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሩዝ፣ ወተት፣ ጭማቂ፣ በናሙና በታዩ መጋዘኖች ተቀምጠው መገኘታቸው፤



**ፎቶ ቁጥር 8፡- ከደረጃ በታች ሆነው መወገድ ሲገባቸው ለረጅም ጊዜ በባለሥልጣኑ መቆጣጠሪያ ኬላዎች መጋዘን የተቀመጡ ምግቦች በከፊል**



ፎቶ ቁጥር 9፡- መወገድ ሲገባቸው ለረጅም ጊዜ በምግብ ማምረቻ መጋዘን የተቀመጡ ምግቦች በከፊል

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ ቃለ መጠይቆች እና በመስክ ምልከታ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

88. የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው መስፈርቱን የማያሟሉ ምግቦች የማስወገድና ወደመጣበት ሀገር የመመለስ ሥራ ሊሠሩ የሚችሉት ገቢዎች ጉምሩክ መሆናቸውን፤የተበላሹ ምግብ ማስወገጃ ቦታዎች እንደ ሀገር ባለመኖራቸው ከፍተኛ የመልካም አስተዳደር ችግር እየፈጠረ መምጣቱን፤ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፤በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት መልስ የገለጹ ሲሆን አወጋገዱ ላይ ምላሽ አልሰጡም፡፡

89. የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምግቦች በአግባቡ ተይዘው እና በህጉ መሰረት መወገዳቸው ካልተረጋገጠ እንዲሁም ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ ምግብ ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ የተደረገው ምግብ በትክክል ስለመመለሱ የማይረጋገጥ ከሆነ ምግቡ እንደገና ተመልሶ ወደ ገበያ እንዲወጣ እና ለህብረተሰቡ እንዲቀርብ በማድረግ ለከፋ የጤና ችግር የሚጋለጥበትን ሁኔታ የሚያመቻች እና ለብልሹ አሰራርና ለሙስና በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

## ምግብ ነክ መረጃዎች በአንድ ማዕከል የሚያዙበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

90. የምግብ ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማትን በሚመለከት ባለሥልጣን መ/ቤቱ መረጃዎች በአንድ ማዕከል የሚያዙበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

91. ይሁን እንጂ የምግብ ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማትን በሚመለከት መረጃ በአንድ ማዕከል የሚያዝበት ስርዓት በባለሥልጣኑ አለመዘርጋቱ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡በኦዲቱ ወቅት ለማየት እንደተቻለው የምግብ ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማትን

- ከብቃት ማረጋገጫ ይሰጠኝ ከሚል መጠየቂያ ጀምሮ በየጊዜው የሚደረጉ ኢንስፔክሽን ሪፖርት ጨምሮ ሁሉም ማስረጃዎች በአንድ ላይ ተይዘው እንዲቀመጡ አለመደረጉ፤

- በናሙና የተመረጡ አምራቾችና የምግብ አስመጪና ላኪዎች ፋይልና ሌሎች ማስረጃዎች ለኦዲቱ እንዲቀርቡ ተጠይቆ ኦዲቱ እሰከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መረጃው ተሟልቶ ያልቀረበ መሆኑ፤

ከቀረበ መጠይቅ እና ከተከለሰ ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ (አባሪ 5 ተያይዟል)

92. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው ሁሉም ማስረጃዎች በኮምፒውተር የተያዙ ሲሆን፣ የፋይል አያያዝን በተመለከተ መዝገብ ቤት ክፍተት ስላለ ወደፊት እንዲስተካከል እየተደረገ ነው በማለት ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት ላይ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ቢሉም ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀ ድረስ በኮምፒዩተር ተያዘ የተባለው ማስረጃ ያልቀረበ ስለሆነ አስተያየቱን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡፡

93. ከምግብ ነክ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሁሉም ማስረጃዎች ተሟልተው እንዲያዙ ካልተደረገ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ምን ያህል የምግብ አምራቾች፣ አስመጪዎችና አከፋፋዮች እንዳሉና ሥራ ላይ ያሉትንና ሥራ ያቆሙ ድርጅቶችን ለይቶ ለማወቅ ያስቸግራል፡፡በተጨማሪም የምግብ ደህንነት ቁጥጥሩ በዕቅድና በመረጃ ላይ እንዳይመሰረት፣የተሟላና ትክክለኛ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

## የኢንስፔክሽንና የምግብ መልቀቂያ የፈቃድ አሰጣጥ ሥራን በተመለከተ፡-

94. በመግቢያና መውጪያ መቆጣጠሪያ ኬላ የኢንስፔክሽንና የምግብ መልቀቂያ የፈቃድ አሰጣጥ ሥራ በተለያየ ቡድን እንዲሰራ ሊደረግ ይገባል፡፡

95. ይሁን እንጂ በመግቢያና መውጪያ መቆጣጠሪያ ኬላ የኢንስፔክሽንና የመልቀቂያ ፈቃድ አሰጣጥ ሥራ በተለያየ ቡድን እንዲሠራ መደረግ ሲገባው ባለጉዳዩ የሚያቀርበው ማመልከቻና ዶክመንት ማለትም (certificate analysis, invoice, bill of loading, packing list, health certificate, declaration) የቀረበለት ባለሙያ የሰነዱን ትክክለኛነት በማረጋገጥ በመቀጠል የመስክ ፍተሻ በማድረግ መልቀቂያ የሚሰጥ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ ቦታዎች በተደረገ የመስክ ምልከታ ከቀረበ መጠይቅና በቀረበው ዶክመንትና ፈቃድ መስጫ ላይ አንድ ባለሙያ ብቻ ከፈረመበት ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

96. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች በአንዳንድ የፍተሻ ጣቢያዎች ባለሙያዎች ለስልጠና እና እረፍት በሚወጡበትና በበላይ ኃላፊ በሚሰጥ ተልእኮ በማይኖሩበት ጊዜ ፍተሻና መልቀቂያ የመስጠት ሥራው በአንድ ሰው

የሚከናወንብት ወቅት መኖሩን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፤በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም በናሙና ተመርጠው በታዩ ሁሉም (አምስቱም) ኬላዎች ላይ የተከለሱ ማስረጃዎች በአንድ ባለሙያ ብቻ የፈቀደ መሆኑን የሚያሳዩ በመሆኑ ያቀረቡትን ምላሽ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

97. በአንድ ሠራተኛ ብቻ በተከናወነ የምግብ ደህንነትና ጥራት ማረጋገጫ ኢንስፔክሽን ማከናወን አግባብ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት ሲባል ለሚፈጸም ሙስና በር የሚከፍት ከመሆኑም በተጨማሪ ጥራቱን ያልጠበቀ ምግብ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባና ተጠቃሚውን ለጤና ችግር የሚያጋልጥ ይሆናል፡፡

## ለክልል የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራ አስፈላጊውን ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፡-

98. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌዴራልና በክልል ያለው የቁጥጥር ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሆን ለማድረግ ለክልል የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራ አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

99. ይሁን እንጂ

- ለክልል የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ የትብብር ሥራ እንዲሠራ አለመደረጉ፣
- የምግብን ደህንነትና ጥራት እንዲጠበቅ ለማድረግ ከክልሎች ጋር በጋራ ለመሥራት እንዲቻል ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ሊደረጉ የሚገባቸው ድጋፎች ማለትም ላብራቶሪ ማደራጀት፣ባለሙያዎችን ማብቃት ሥራ የማይከናወን መሆኑ፣
- ምግብን በተመለከተ በክልሎች ስለአለው እንቅስቃሴ፣ሰለተፈጠሩ ችግሮች እና መወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ቢያንስ በሪፖርት መልክ ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ጋር የማይለዋወጡ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ ክልሎች በተደረገ የመስክ ምልከታ፣ከቀረበ መጠይቅና ከተከለሰ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

100. የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በየዓመቱ ለክልል ጤና ተቆጣጣሪ አካላት ድጋፍ እየተደረገ ነው ለዚህም ቀሪ ሪፖርት ማየት ይቻላል በማለት ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት ላይ ገልጸዋል፡፡ኃላፊው ድጋፍ እያደረግን ነው ቢሉም ለክልሎች ስለተደረገ ድጋፍ የሚገልጽ ማስረጃም ሆነ ሪፖርት ኦዲቱ እስከተጠናቀቀ ድረስ አልቀረበም፡፡

101. የምግብ ደህንነትና ጥራትን ለማስጠበቅ የሚሠራ ሥራ በባለሥልጣን መ/ቤቱ ብቻ መሰከናወን የማይቻል እና ምግብ የሚመረተው፣ከውጭ የሚገባውም ሆነ የሚከፋፈለው በአገሪቱ ባሉ ክልሎች፣ ከተሞችና ገጠሮች እንደመሆኑ መጠን በነዚህ ቦታዎች ምን እየተሠራ መሆኑን ማወቅና ተገቢውን ድጋፍ  ባለሥልጣኑ የማድረግ ኃላፊነቱን አለመወጣቱ እና በየክልሉ የሚገኙ የምግብ ደህንነትና ጥራት ቁጥጥርን በአስተባባሪነት አለመምራቱ  በሚፈለገው መጠን  ውጤት የማይገኝ እና ህብረተሰቡ በሚቀርብለት ምግብ ተጠቃሚ ከመሆን ይልቅ ተጎጂ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

### መደምደሚያ

102. የምግብ ደህንነት ቁጥጥር አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን እና የታሰበውን ዓላማ ማሳካት የተቻለ መሆኑን በተመለከተ የሚከተሉት የአሠራር ግድፈቶች እና ክፍተቶች ተገኝተዋል፡፡

- ለምግብ አምራች ድርጅቶች፣ለጥራት መቆጣጠሪያ ላብራቶሪዎች ለአስመጪዎች፣ ለላኪዎች፣ ለአከማችና ለአከፋፋይ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፣ ማደስ፣ማገድ እና መሰረዝ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ ፤

- ማንኛውም ምግብ ሲመረት፣ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ፣ ወደ ውጭ ሲላክ፣ ሲዘጋጅ፣ ሲከማች፣ ሲከፋፈል፣ሲጓጓዝ፣ሲሸጥ ወይም ለህብረተሰቡ ሲቀርብ ባለስልጣን መ/ቤቱ እንዲያውቀውና ፈቃድ እንዲያገኝ አለመደረጉ፤
- ከውጭ አገር ለሚገባም ሆነ በአገር ውስጥ ለሚመረት ማንኛውም ምግብ፤ የምግብ ምዝገባ ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤
- ማንኛውም የምግብ ንግድ ድርጅት የድርጅቱን ሥምና አድራሻ የያዘ የውጭ ማስታወቂያ ቢያንስ በአማርኛ ቋንቋ ጽፎ ድርጅቱ በሚገኝበት ቦታ የለጠፈ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ያልተደረገ መሆኑ፤

- ማንኛውም የምግብ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት ቶሎ ሊበላሽ የሚችል ምግብን በሚያከማችበት፣ ለዕይታ በሚያቀርብበት፣ በሚያሽግበት ወይም በሚያጓጉዝበት ጊዜ ምግቡ በተገቢው የሙቀት መጠን ወይም የቅዝቃዜ ሰንሰለት ውስጥ መሆኑ የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

- እንደሥራው ባህሪ ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች የግል ንጽህናቸው እንዲጠበቅ በማድረግ በሥራ ወቅት የምግብን ጥራትና ደህንነት መጠበቂያ አልባሳት የሚያደርጉ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ያልተደረገ መሆኑ፤

- በማንኛውም የምግብ ማምረቻ ድርጅት በሚደረግ ኢንስፔክሽን ወቅት የሚገኙ ማንኛውም ክፍተቶች በኢንስፔክሽን ቼክ ሊስት ተሞልተው የግምገማ ነጥባቸው ከፋይላቸው ጋር ሊያያዝና የግምገማው ነጥብ ኮፒው ለድርጅቶቹ እንዲሰጥ አለመደረጉ፤

- ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የምግብ ጥራት ምርመራ ላብራቶሪዎች በማደራጅት ሥራ ላይ እንዲውሉ ያላደረገ መሆኑ ፤
- በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምግቦችን ጥራት ለማረጋገጥ የፊዝኮኬሚካል፣ የማይክሮባዮሎጂና የቶክሲኮሎጂ ምርምራ የማይደረግ መሆኑ፤
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በምግብ መመረዝ ወይም መበከል ምክንያት ለሚደርስ የሞትና የጤንነት መታወክ መንስኤ የሆነውን ንጥረ ነገር ልዩ ልዩ ናሙናዎችን በመውሰድ ወይም በመቀበል መርምሮ ምንነታቸውን የሚያረጋግጥበትና አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፤
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የተከለሱ፣የተበላሹ፣የተጭበረበሩ፣የተበከሉ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብለው በተጠረጠሩ ምግቦች ላይ የላብራቶሪ ምርመራ እንዲካሄድ በማድረግ ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስም በአገልግሎት ላይ እንዳይውሉ ታሽገው እንዲቆዩ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ማንኛውም ምግብ በምርቱ የመጀመሪያ ማሸጊያ (Primary Packing) ላይ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የተፃፈ ሆኖ በግልጽ የሚነበብና በቀላሉ የማይለቅ የምግቡን ይዘት ብቻ የሚገልጽ ጽሁፍ መሆኑ እንዲረጋገጥ አለመደረጉ፤
- ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ የምግብ ጥሬዕቃዎችና የማሸጊያ ቁሳቁሶች ላይ ቁጥጥር በማካሄድ የመግቢያና የሙውጫ ፈቃድ የሚሰጥበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤
- በሀገር ደረጃ በህጋዊ መንገድ ለህብረተሰቡ እየቀረቡ ለሚገኙት ምግቦች የምግብ ዝርዝር በማደራጀት በገበያ ላይ ያሉ ህጋዊና ህገወጥ ምግቦች እንዲለዩ አለመደረጉ፤
- የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምግቦች እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ ተቆጥረውና ተመዝግበው እንዲሁም ከሌሎች ምግቦች ተለይተው ጥቅም ላይ እንደማይውሉ የሚገልጽ ጽሁፍ በመለጠፍ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቦታ እንዲከማቹ ክትትልና ቁጥጥር ያልተደረገ መሆኑ፤
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ፣ የአገልግሎት ጊዜው ያበቃ ምግብና ጥሬ ዕቃ ደህንነቱና ጥራቱ ያልተጠበቀ መሆኑ ከተረጋገጠ አግባብ ባለው መንገድ እንዲወገድ ወይም ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

- የምግብ ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማትን በሚመለከት ባለሥልጣን መ/ቤቱ መረጃዎች በአንድ ማዕከል የሚያዙበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤
- በመግቢያና መውጪያ መቆጣጠሪያ ኬላ  የኢንስፔክሽንና የምግብ መልቀቂያ የፈቃድ አሰጣጥ ሥራ በተለያየ ቡድን እንዲሰራ አለመደረጉ፤
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በፌዴራልና በክልል ያለው የቁጥጥር ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሆን ለማድረግ ለክልል የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራ አስፈላጊውን ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፤ታውቋል፡፡

ስለሆነም በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ሊያሻሽሉ ይችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

**ክፍል አራት**

***የማሻሻያ ሀሳብ፤-***

103. *ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የምግብ ደህንነት ጥራት ቁጥጥርን በቁጠባ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-*

- *ባለሥልጣን መ/ቤቱ የምግቦችን ደህንነትና ጥራት ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማትን የቁጥጥር ደረጃዎች አዘጋጅቶለምግብ አምራች ድርጅቶች፣ለጥራት መቆጣጠሪያ ላብራቶሪዎች፣ ለአስመጪዎች፣ ለላኪዎች፣ ለአከማችና ለአከፋፋይ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፣ማደስ፣ ማገድ እና መሰረዝ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እንዲሆንና ማንኛውም ምግብ ሲመረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ፣ ወደ ውጭ ሲላክ፣ ሲዘጋጅ፣ ሲከማች፣ ሲከፋፈል፣ ሲጓጓዝ፣ ሲሸጥ ወይም ለህብረተሰቡ ሲቀርብ ባለሥልጣን መ/ቤቱ እንዲያውቀውና ፈቃድ እንዲያገኝ በማድረግ ከውጭ አገር ለሚገባም ሆነ በአገር ውስጥ ለሚመረት ማንኛውም ምግብ፤ የምግብ ምዝገባ ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡*

- *ማንኛውም የምግብ ንግድ ድርጅት የድርጅቱን ሥምና አድራሻ የያዘ የውጭ ማስታወቂያ ቢያንስ በአማርኛ ቋንቋ ጽፎ ድርጅቱ በሚገኝበት ቦታ የለጠፈ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡*

- *ማንኛውም የምግብ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት ቶሎ ሊበላሽ የሚችል ምግብን በሚያከማችበት፣ ለዕይታ በሚያቀርብበት፣ በሚያሽግበት ወይም በሚያጓጉዝበት ጊዜ ምግቡ በተገቢው የሙቀት መጠን ወይም የቅዝቃዜ ሰንሰለት ውስጥ መሆኑ የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ስለማድረጉ በባለሥልጣኑ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡*

- *ባለሥልጣኑ እንደሥራው ባህሪ ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች የግል ንጽህናቸው እንዲጠበቅ በማድረግ በሥራ ወቅት የምግብን ጥራትና ደህንነት መጠበቂያ አልባሳት የሚያደርጉ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በማንኛውም የምግብ ማምረቻ ድርጅት በሚደረግ ኢንስፔክሽን ወቅት የሚገኙ ማንኛውም ክፍተቶች በኢንስፔክሽን ቼክ ሊስት ተሞልተው የግምገማ ነጥባቸው*

ከፋይላቸው ጋር እንዲያያዝና የግምገማው ነጥብ ኮፒው ለድርጅቶቹ መሰጠት አለበት፡፡

❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የምግብ ጥራት ምርመራ ላብራቶሪዎች በማደራጀት ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
❖ በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምግቦችን ጥራት ለማረጋገጥ የፊዝኮኬሚካል፣ የማይክሮባዮሎጂና የቶክሲኮሎጂ ምርምራ በማድረግ በምግብ መመረዝ ወይም መበከል ምክንያት ለሚደርስ የሞትና የጤንነት መታወክ መንስኤ የሆነውን ንጥረ ነገር ልዩ ልዩ ናሙናዎችን በመውሰድ ወይም በመቀበል መርምሮ ምንነታቸውን የሚያረጋግጥበትና አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ የተከለሱ፣የተበላሹ፣የተጭበረበሩ፣የተበከሉ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብለው በተጠረጠሩ ምግቦች ላይ የላቦራቶሪ ምርመራ እንዲካሄድ በማድረግ ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስም በአገልግሎት ላይ እንዳይውሉ ታሽገው እንዲቆዩ ሊያደርግ ይገባል፡፡
❖ ማንኛውም ምግብ በምርቱ የመጀመሪያ ማሸጊያ (Primary Packing) ላይ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የተፃፈ ሆኖ በግልጽ የሚነበብና በቀላሉ የማይለቅ የምግቡን ይዘት ብቻ የሚገልጽ ጽሁፍ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

❖ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ የምግብ ጥሬዕቃዎችና የማሸጊያ ቁሳቁሶች ላይ ቁጥጥር በማካሄድ የመግቢያና የሙውጫ ፈቃድ የሚሰጥበት ስርዓትሊዘረጋ ይገባል፡፡
❖ በሀገር ደረጃ በህጋዊ መንገድ ለህብረተሰቡ እየቀረቡ ለሚገኙት ምግቦች የምግብ ዝርዝር በማደራጀት በገበያ ላይ ያሉ ህጋዊና ህገወጥ ምግቦች እንዲለዩና የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምግቦች እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ ተቆጥረውና ተመዝግበው እንዲሁም ከሌሎች ምግቦች ተለይተው ጥቅም ላይ እንደማይውሉ የሚገልጽ ጽሁፍ በመለጠፍ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቦታ እንዲከማቹ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ፣ የአገልግሎት ጊዜው ያበቃ ምግብና ጥሬ ዕቃ ደህንነቱና ጥራቱ ያልተጠበቀ መሆኑ ከተረጋገጠ አግባብ ባለው መንገድ እንዲወገድ ወይም ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የምግብ ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማትን በሚመለከት ባለሥልጣን መ/ቤቱ መረጃዎች በአንድ ማዕከል የሚያዙበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በመግቢያና መውጪያ መቆጣጠሪያ ኬላ የኢንስፔክሽንና የምግብ መልቀቂያ የፈቃድ አሰጣጥ ሥራ በተለያየ ቡድን እንዲሰራ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በፌዴራልና በክልል ያለው የቁጥጥር ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሆን ለማድረግ ለክልል የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራ አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደረግ ይገባል፡፡
- በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን፤የምግብ ደህንነትና ጥራት ቁጥጥርን አስመልክቶ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት ለሚያከናውነው የምግብ ደህንነትና ጥራት ቁጥጥር ማንኛውም ምግብ ሲመረት፣ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ፣ ወደ ውጭ ሲላክ፣ ሲዘጋጅ፣ ሲከማች፣ ሲከፋፈል፣ሲጓጓዝ፣ሲሸጥ ወይም ለገበያ ሲቀርብ ባለስልጣን መ/ቤቱ እንዲያውቀውና ፈቃድ እንዲያገኝና የምግቡን ደህንነትና ጥራት ቁጥጥር ቢያደረግ ህብረተሰቡ ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ ምግብ ያገኛል፡፡
- በዚህ ሪፖርት የተገለጹት ግኝቶች፣ መደምደሚያዎች እና የማሻሻያ ሀሳቦች ባለሥልጣን መ/ቤቱ በዋነኛነት የተቋቋመበትን ዓላማና ኃላፊነት ለመወጣት ስለሚያግዘው በተጠቀሱት ችግሮች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ በማመቻቸት በአዋጁ እና በደንቡ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት ጉዳዩን በማሳወቅ፣ በመከታተልና በመቆጣጠር ኃላፊነቱን መወጣት ይጠበቅበታል፡፡
- በመጨረሻም የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን፤እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው ፌዴራል መ/ቤቶች፣ የምግብ ደህንነትና ጥራት ቁጥጥር የሚመለከታቸው በናሙና የታዩ የክልል የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ አንድ፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት


| **የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ** (Audit Issues) | **የኦዲት መመዘኛ መስፈርት** *(Evaluative Criteria)* |
|---|---|
| 1. **ለምግብአምራቾች፤ ላኪዎች፤አስመጪዎችና አከፋፋዮች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥና የምግብ ምዝገባ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤** | 1. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለምግብ አምራች ድርጅቶች፣ለጥራት መቆጣጠሪያ ላቦራቶሪዎች፣ ለአስመጪዎች፣ ለላኪዎች፣ ለአከማችና ለአከፋፋይ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፣ ማደስ፣ ማገድ እና መሰረዝ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 2. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለምግብ አምራቾች የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን በማካሄድ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 3. ማንኛውም ምግብ ሲመረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ፣ ወደ ውጭ ሲላክ፣ ሲዘጋጅ፣ ሲከማች፣ ሲከፋፈል፣ ሲጓጓዝ፣ ሲሸጥ ወይም ለህብረተሰቡ ሲቀርብ ባለስልጣን መ/ቤቱ እንዲያውቀውና ፈቃድ እንዲያገኝ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 4. ባለስልጣን መ/ቤቱ ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው የምግብ አገልግሎት ተቋም አለማካሄዱን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 5. ባለስልጣንመ/ቤቱየምግብአገልግሎትተቋምለሚያካሂድአካልየሰጠውየ ብቃትማረጋገጫየምስክርወረቀት በየዓመቱ መታደሱን ሊቆጣጠርይገባል፡፡ |
| | 6. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የምግብ አምራች፣ አስመጪና አከፋፋይ ድርጅቶች ፈቃድ ባለማሳደሳቸው እንዲጠየቁ የሚያደርግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 7. ከውጭ አገር ለሚገባም ሆነ በአገር ውስጥ ለሚመረት ማንኛውም ምግብ፤ የምግብ ምዝገባ ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 8. ምግብን ለማስመዝገብየሚቀርቡሰነዶችሁሉብአማርኛወይም በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተጻፉ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 9. ማንኛውም ለምዝገባ የሚቀርብ ምግብ በሀገር አቀፍ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የደህንነት መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 10. ባለስልጣን መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ እና ሕገወጥ ምግቦችን የሚቆጣጠርበትና እርምጃ የሚወስድበት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 11. ማንኛውም የመደበኛ አመጋገብን ንጥረ ምግብ ፍላጎት ለማሟላት የሚዘጋጅ ንጥረ ምግብ (የምግብ ማሟያ)ለሽያጭ ከመቅረቡ በፊት ተጨማሪ ምግቡ ተመዝግቦ ፈቃድ እንዲሰጠው ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 12. ማንኛውም የተመዘገበ ምግብ በምርቱ ይዘትና ማሸጊያ ላይ ለውጥ ካልተደረገበት በስተቀር ምዝገባው በየአራት ዓመት መታደስ አለበት፡፡ |
| 2. **የምግብ ማምረቻዎች የመልካም አመራረት ሥርዓት ቁጥጥር ገ መደረጉን ማረጋገጥ፤** | 13. ማንኛውምየምግብንግድድርጅትየድርጅቱንሥምናአድራሻ የያዘየውጭማስታወቂያቢ.ያንስበአማርኛቋንቋጽፎድርጅቱበሚገኝበትቦ ታ የለጠፈ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 14. ማንኛውም የምግብ ንግድ ድርጅት የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የዋናውን ቅጅ በግልጽ በሚታይ ቦታ ያስቀመጠ |

| | |
|---|---|
| | ስለመሆኑ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 15. በምግብ አምራች፤ላኪ፣አስመጪና አከፋፋይ ድርጅት ውስጥ ለሚከናወኑ ተግባራት የአሰራር ስርአት (Standard Operating Procedure) መኖሩ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 16. ባለስልጣን መ/ቤቱ ማንኛውም የምግብ ማምረቻ ድርጅት ፈቃድ ሳያገኝና ሳያስመዘግብ በምግብ ማምረቻ ተቋሙ የምርት አይነትና ሂደት ላይ ለውጥ አለማድረጉን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 17. ማንኛውም ምግብ ባለስልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን ወይም የተቀበለውን መስፈርት ተከትሎ ጤናማ አጠባበቅ እየተደረገለት ስለመሆኑ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 18. ማንኛውም ምግብን በማምረት፣ በማዘጋጀት፣ በማከማቸት፣ በማከፋፈልና በማጓጓዝ ሥራ ላይ የተሰማራ ተቋም ከምርቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሠራተኞች በተላላፊ በሽታ የተያዙ አለመሆናቸው እንዲረጋገጥ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 19. ባለስልጣን መ/ቤቱ ማንኛውም የምግብ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት ቶሎ ሊበላሽ የሚችል ምግብን በሚያከማችበት፣ ለዕይታ በሚያቀርብበት፣ በሚያሽግበት ወይም በሚያጓጉዝበት ጊዜ ምግቡ በተገቢው የሙቀት መጠን ወይም የቅዝቃዜ ሰንሰለት ውስጥ መሆኑ የሚረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 20. ባለስልጣን መ/ቤቱ ማንኛውም የምግብ አምራች፣ላኪ፣አስመጪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት ምግብን በሚያከማችበት፣ በሚጭንበት፣ ወይም በሚያጓጉዝበት ጊዜ ከምግቡ ጋር ንክኪ የሚኖረው ክፍል ንፁህ እና ለማንኛውም ጎጂ ለሆኑ ነገሮች ያልተጋለጠ መሆኑን የሚቆጣጠርበት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 21. ከምግብ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች የግል ንጽህናቸው እንዲጠበቅ በማድረግ እንደሥራው ባህሪ በሥራ ወቅት የምግብን ጥራትና ደህንነት መጠበቂያ አልባሳት የሚያደርጉ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 22. በምግብ ማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች በመመሪያው መሰረት የሥራ መደቡ የሚጠይቀውን ተፈላጊ ችሎታና ሙያ የሚያሟላ ባለሙያ ቀጥረው ማሰራታቸውን ባለስልጣን መ/ቤቱ ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| | 23. በማንኛውም የምግብ ማምረቻ ድርጅት በሚደረግ ኢንስፔክሽን ወቅት የሚገኙ ማንኛውም ክፍተቶች በኢንስፔክሽን ቼክ ሊስት ተሞልተው የግምገማ ነጥባቸው ከፋይላቸው ጋር ሊያያዝና የግምገማው ነጥብ ኮፒው ለድርጅቶቹ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 24. የምግብ ንግድ ማስታወቂያ በመገናኛ ብዙሀን ወይም በማናቸውም መንገድ ሲተላለፍ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መመሪያ መሰረት መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 25. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የምግብ ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪዎች ሊያደራጅና ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡ |
| **3. የቅድመና የድህረ ገበያ ቁጥጥር(ኢንስፔክሽን) ስርዓት ተዘርግቶገግባራዊ መደረጉን ገ ማረጋገጥ፤** | 26. ምግብ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ በሀገሪቱ ባሉ የመግቢያና መውጫ ኬላዎች ብቻ ሆኖ፤ አስፈላጊው የጥራትና የደህንነት ፍተሻ በባለሥልጣን መ/ቤቱ ሲከናወን ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 27. ማንኛውም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ የምግብ ምርት በሚመለከተው |

| | |
|---|---|
| | የላኪው ሀገር የመንግሥት አካል የተረጋገጠ የጥራትና የጤናማነት ሰርተፊኬት አብሮት እንዲመጣ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 28. በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምግቦችን ጥራት ለማረጋገጥ የፊዝኮኬሚካል፣ የማይክሮባዮሎጂና የቶክሲኮሎጂምርምራ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 29. ማንኛውም ምግብ በምርቱ የመጀመሪያ ማሸጊያ (Primary Packing) ላይ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የተፃፈ ሆኖ በግልጽ የሚነበብና በቀላሉ የማይለቅ ገላጭ ጽሁፍ ያለው ስለመሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 30. ማንኛውም የምግብ ገላጭ ጽሑፍ አቀራረብ የምግቡን ይዘት ብቻ የሚገልጽ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 31. ባለስልጣን መ/ቤቱ ማንኛውንም ምግብ ከማንኛውም የሰውን ጤና ሊጎዳ ከሚችል ወይም የምግቡን ጥራትና ደህንነት ሊያጓድል ከሚችል ነገር ጋር በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ አለመደባለቁን የሚያረጋግጥበት የቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 32. ባለስልጣን መ/ቤቱወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ የምግብ ጥሬዕቃዎችና የማሸጊያ ቁሳቁሶች ላይ ቁጥጥር በማካሄድ የመግቢያና የሙውጫ ፈቃድ የሚሰጥበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 33. በሀገር ደረጃ በህጋዊ መንገድ ለህብረተሰቡ እየቀረቡ ለሚገኙት ምግቦች የምግብ ዝርዝር በማደራጀት በገበያ ላይ ያሉ ህጋዊና ህገወጥ ምግቦች እንዲለዩ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 34. የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ምግቦች እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ ተቆጥረውና ተመዝግበው እንዲሁም ከሌሎች ምግቦች ተለይተ ው ጥቅም ላይ እንደማይውሉ የሚገልጽ ጽሁፍ በመለጠፍ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቦታ የተከማቸ መሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግበትይገባል፡፡ |
| | 35. የምግብ አምራች፤ አስመጪ፤ አከፋፋይና አጓጓዥ ድርጅቶች በኢንስፔክሽን ወቅት በፈረሙት የሙተማመኛ ስምምነት መሰረት የገቡትን ግዴታ በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ማስተካከያ ስለማድረጋቸው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 36. በእያንዳንዱ የምግብ ምርት ዓይነትና መጋዘን ላይ የምርቱን ዓይነት፣ ምርቱ ያለበትን ሁኔታ (አያያዝ፣ አቀማመጥና የቆይታ ጊዜው ያለበትን ደረጃ) እና ሌሎች ስለምግቡ የሚገልጹ መረጃዎች በየጊዜው ስለመለጠፋቸው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 37. ባለስልጣን መ/ቤቱ ማንኛውም የምግብ ማሸጊያ፣መለያ፣የንግድ ምልክት፣የንግድ ስም ወይም ማንኛውም ዓይነትልዩ ምልክት በመጠቀም ምግቡ በእውነተኛው አምራች እንደተመረተ በማስመሰል ወይም የምግቡ ጥራትና ደህንነት ተጓድሎ እንዳይቀርብ የሚቆጣጠርበት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 38. ባለስልጣን መ/ቤቱ የምግብ ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማትን በሚመለከት መረጃዎች በአንድ ማዕከል የሚያዙበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 39. ባለስልጣን መ/ቤቱ በምግብ መመረዝ ወይም መበከል ምክንያት ለሚደርስ የሞትና የጤንነት መታወክ መንስኤ የሆነውን ንጥረ ነገር |

| | |
|---|---|
| | ልዩ ልዩ ናሙናዎችን በመውሰድ ወይም በመቀበል መርምሮ ምንነታቸውን የሚያረጋግጥበትና አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 40. ባለስልጣን መ/ቤቱ የተከለሱ፣ የተበላሹ፣ የተጭበረበሩ፣ የተበከሉ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብለው በተጠረጠሩ ምግቦች ላይ የላቦራቶሪ ምርመራ እንዲካሄድ ማድረግና ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስም በአገልግሎት ላይ እንዳይውሉ ታሽገው እንዲቆዩ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 41. ባለስልጣን መ/ቤቱ ገበያ ላይ የዋሉ ምግቦችን ደህንነት እና ጥራት ለማረጋገጥ የድህረ ገበያ ቅኝትና ተገቢውን የቁጥጥር ሥራ በማካሄድ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ |
| | 42. ባለስልጣን መ/ቤቱ በፌዴራልና በክልል ያለው የቁጥጥር ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሆን ለማድረግ ለክልል የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራ አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 43. በመግቢያና መውጪያ መቆጣጠሪያ ኬላ እና የምግብ ፋብሪካዎች የኢንስፔክሽንና የፈቃድ አሰጣጥ ሥራ በተለያየ ቡድን እንዲሰራ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 44. ባለስልጣን መ/ቤቱ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ምግቦችና ጥሬ ዕቃዎች መወገዳቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 45. ባለስልጣን መ/ቤቱ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ እና ከውጭ አገር የገባ ምግብ ደህንነቱና ጥራቱ ያልተጠበቀ መሆኑን ካረጋገጠ አግባብ ባለው መንገድ እንዲወገድ ወይም ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 46. በሀገር ውስጥ ለሚወገድ ምግብ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ተቆጣጣሪዎች በተገኙበት በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አዋጅና ደንብ መሠረት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መስሪያቤቶች በተውጣጣ ኮሚቴ አማካይነት አካባቢያዊ ተጽዕኖ በማያሳድር መልኩ እንዲወገድ የተደረገ ስለመሆኑ ሪፖርት እንዲቀርብ ሊደረግ ይገባል፡፡ |

አባሪ 2፡ የባለሥልጣኑ ድርጅታዊ መዋቅር /ORGANAISATIONAL STRUCTURE OF FMHACA/



## አባሪ 3፡ በናሙና የታዩ የመንግሥትና የግል ተቋማት

| | |
|---|---|
| 1 | በኢትዮጵያ የምግብ የመድሀኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን |
| 2 | በማዕከላዊ ቅርንጫፍ ቃሊቲ  መግቢያና መውጫ ኬላ |
| 3 | በማዕከላዊ ቅርንጫፍ ኤርፖርት ካርጎ መግቢያና መውጫ ኬላ |
| 4 | በማዕከላዊ ቅርንጫፍ ቦሌ ኤርፖርት ተርሚናል መግቢያና መውጫ ኬላ |
| 5 | ሞጆ ጤና ኳራንቲን ጣቢያ |
| 6 | አዳማ ጤና ኳራንቲን ጣቢያ |
| 7 | በፓስተር የምግብ ጥራት ምርመራ ዳይሬክቶሬት |
| 8 | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የም/የመ/ጤ/ክ/አሰ/ቁ/ባለስልጣን |
| 9 | አዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ |
| 10 | በኦሮሚያ ጤና ቢሮ |
| 11 | አፍሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 12 | አዲስ ሞጆ የምግብ ዘይት ኮምፕሌክስ አክስዮን ማህበር |
| 13 | ሆላንድ ዴየሪ ኃ/የተ/የግ/ማሕበር |
| 14 | ገትስ አግሮ ኢንዱስትሪ |
| 15 | አህዱክስ ፉድ ፕሮዳክትስ ኢ.ማ |
| 16 | በሲልቫ አልኮልና ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ |
| 17 | ኢስት አፍሪካን ታይገር ብራንድስ ኢንዱስትሪ ፒ.ኤል.ሲ |
| 18 | ጀነሲስ ፋርም |
| 19 | ለገጣፎ ብሌስ አግሪ ፉድስ ላቦራቶሪ |

## አባሪ 4፡ በባለስልጣን መ/ቤቱ ድህረ ኢንስፔክሽን ሳይደረግ ፈቃዳቸው የታደሰ ድርጅቶች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የድርጅቱ ስም | በቀጥታ የሚታደስ | በኢንስፔክሽን የሚታደስ | የኢንስፔክሽን ቼክ ሊስት | የኢንስፔክሽን ሪፖርት | በኢንስፔክሽን ሪፖርት መሰረት ማስተካከያ ስለመድረጉ የተካሄደ ቁጥጥር | ፈቃዱ የታደሰበት ዓ.ም | የመተማመኛ ሰነድ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኢትዮ ታካሞል ኢንደስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ | በቀጥታ | | የለም | 27/10/08 እና 5/11/08 የተሰራ | የለም | 2009 | የለም |
| 2 | ሎኒ አግሮ ኢንደስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ | በቀጥታ | | የለም | በ01/12/09 የእገዳ ደብዳቤ | የለም | 2009 | የለም |
| 3 | ናታ ወተትና የወተት ተዋፅኦ መፈብረክ | | በኢንስፔክሽን | የለም | 07/07/08 | የለም | 2009 | የለም |
| 4 | ዳይመንድ መጠጦች ፕሮዳክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ | | በኢንስፔክሽን | የለም | 20/03/08 | የለም | 2008 | የለም |
| 5 | ስዊትስ ወርልድ ኮንፌክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ | በቀጥታ | | የለም | 20/10/09 | የለም | 2010 | የለም |
| 6 | ሀላዋ ከረሚላ ፋብሪካ | በቀጥታ | | የለም | የለም | የለም | 2010 | የለም |
| *7* | *ኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ ሼር ካምፓኒ* | | *በኢንስፔክሽን* | *የለም* | ***11/12/2014 24/10/07*** *ማስጠንቀቂያ ተፅፏል* | *የለም* | ***2009*** | *የለም* |
| 8 | አፍራን ግሎባል ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማ | በቀጥታ | | የለም | 01/7/2015 | የለም | 2009 | የለም |
| 9 | አግማስ ማኑፋክቸሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ | በቀጥታ | | የለም | 02/12/06 | የለም | 2009 | የለም |
| 10 | አባሃዋ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ | በቀጥታ | | የለም | 27/01/08 | የለም | 2009 | የለም |
| 11 | አኹ-ዋን የምግብ ኮምፕሌክስ | በቀጥታ | | የለም | 20/1/2009 | የለም | 2010 | የለም |
| 12 | ሰበታ አግሮ ኢንደስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ | በቀጥታ | | የለም | የለም | የለም | 2009 | የለም |
| 13 | መልካም እንዳለ የወተት ፋብሪካ | | በኢንስፔክሽን | የለም | ጊዜያዊ የዕገዳ ደብዳቤ 17/12/09 | የለም | 2010 | የለም |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ሂባ ከረሜላ ማምረቻ ፋብሪካ | | በኢንስፔክሽን | | Pre-ins.15/4/09 | ዳግም ኢንስፔክሽን 08/12/2009 | 2010 | የለም |
| 15 | ባለዛፍ አልኮልና መጠጥ ፋብሪካ | በቀጥታ | | የለም | የለም | የለም | 2010 | የለም |
| 16 | ቦኤዝ የምግብ ኮምፕሌክስ ኃ/የተ/የግ/ማ | | በኢንስፔክሽን | የለም | 22/03/2007 | የለም | 2008 | የለም |
| 17 | ሆራ የምግብ ኮምፕሌክስ ኃ/የተ/የግ/ማ | በቀጥታ | | የለም | 16/05/13 | 15/02/06 የተሰራ ፍተሻ | 2009 | የለም |
| 18 | ደብረ ዘይት አሳማ እርባታ የስጋ ማቀነባበሪያ | በቀጥታ | | የለም | 03/09/09 | የለም | 2010 | የለም |
| 19 | ማፕል ዲስትለሪ ኃ/የተ/የግ/ማ | በቀጥታ | | የለም | የለም | የለም | 2009 | የለም |
| 20 | ፓስፊክ ኢንደስትሪዎች ኃ/የተ/የግ/ማ (የታሸገውሃ አምራች) | | በኢንስፔክሽን | የለም | የለም | የለም | 2010 | የለም |
| 21 | ፓስፊክ ኢንደስትሪዎች ኃ/ የተ/ የግ/ ማ (የጁስ ማቀነባበሪያ) | | | የለም | የለም | የለም | 2009 | የለም |
| 22 | ኪንግ አልኮል ማምረቻ | | በኢንስፔክሽን | የለም | የለም | የለም | 2010 | የለም |
| 23 | አባይ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማ(አልሚ ምግብ አምራች) | በቀጥታ | | የለም | የለም | የለም | 2010 | የለም |
| 24 | ኢንሪች አግሮ ኢንደስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ | | በኢንስፔክሽን | የለም | 11/02/2007 | የለም | 2009 | የለም |
| 25 | ሄለን ሐሰን ከረሜላ ማምረቻ | በቀጥታ | | የለም | የለም | የለም | 2010 | የለም |
| 26 | አዲስ ሞጆ የምግብ ዘይት ኮምፕሌክስ አ.ማ(ሞጆ እና አዲስ አበባ) | | በኢንስፔክሽን | የለም | የለም | የለም | 2010 | የለም |
| 27 | ግሬት አቢሲኒያ ኃ/የተ/የግ/ማ(ጁስና ለስላሳ መጠጥ አምራች) | | በኢንስፔክሽን | የለም | የለም | ጊዜያዊ ዕገዳን ስለማንሳት ብቻ የተፃፈ | 2010 | የለም |
| 28 | ይመር አሊ መሀመድ ምግብ አከፋፋይ | | | 05/12/08 | የለም | የለም(የተሟላ የባለሙያ መረጃ የለም) | 2010 | አለ |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 29 | ፉድ ካም ጀነራል ትሬዲንግ(ምግብ አስመጪ) | | | የለም | የለም | የለም | 2006 | የለም |
| 30 | ፉአድ አሊ(ፍቃድ የመለሰ 8/5/09) | | | የለም | የለም | የለም | 2009 | የለም |
| 31 | አፍሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (ፓስታና ማካሮኒ አምራች | በቀጥታ | | | | የለም | 2009 | |
| 32 | ሆላንድ ዴየሪ ኃ/የተ/የግ/ማሕበር | | በኢንስፔክሽን | | | የለም | 2009 | |
| 33 | አሀዱክስ ፉድ ፕሮዳክትስ ኢ.ማ | በቀጥታ | | | | የለም | 2009 | |
| 34 | ኢስት አፍሪካን ታይገር ብራንድስ ኢንዱስትሪ ፒ.ኤል.ሲ | በቀጥታ | | | | የለም | 2009 | |
| 35 | ሲልቫ አልኮልና ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ | | በኢንስፔክሽን | የለም | | የለም | 2010 | |
| 36 | ለጀነሲስ ፋርም | | | የለም | | የለም | ፈቃድ የለውም | |
| 37 | ገትስ አግሮ ኢንዱስትሪ | | | የለም | | | 2009 | የለም |

## አባሪ 5፡ የተከለሱ የአምራች ድርጅቶች ፋይል ዝርዝር (የቀረቡና ያልቀረቡ)

| ተ.ቁ | የሚፈለጉ ማስረጃዎች | የቀረበ | ያልቀረበ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Abay international | √ | | |
| 2 | Ahwan food complex | √ | | |
| 3 | Horra Food Complex Plc | √ | | |
| 4 | Sweet Honey | | √ | |
| 5 | Agape flour factory | | √ | |
| 6 | Alhamdu flour factory | | √ | |
| 7 | Boaze pasta and macaroni | √ | | |
| 8 | Enrich Agro Industry Plc | √ | | |
| 9 | Lina Bakery Industry | | √ | |
| 10 | Elfora Agro industries | | √ | |
| 11 | Akesekar Ethiopia Casing plc | | √ | |
| 12 | D/Zeyte sewayme | √ | | |
| 13 | Bese general trading PLC | | √ | |
| 14 | Health care food manufacturing | | √ | |
| 15 | Nabta oil processing | | √ | |
| 16 | Addis Mojo ediblBalezaf Alcohol Factory | √ | | |
| 17 | Balezaf Alcohol Factory | √ | | |
| 18 | Mapple Distilleries plc | √ | | |
| 19 | Sit. Gorge Brewery | | √ | |
| 20 | King Alcohol And Liquor Factory | √ | | |
| 21 | ES Alcohol beverage | | √ | |
| 22 | Diamond Beverage production oil | √ | | |
| 23 | Afran global business PLC | √ | | |
| 24 | ethio tekamol | √ | | |
| 25 | zeday agro industry | | √ | |
| 26 | Merti Fruit and vegetable processing | | √ | |
| 27 | Great abyssinia PLC | √ | | |
| 28 | Pacific industries | √ | | |
| 29 | East Africa Bottling | √ | | |
| 30 | Abahawa Trading plc | √ | | |
| 31 | Agmas water manufacturing plc | √ | | |
| 32 | Ambo mineral water plc | | √ | |
| 33 | Deble S Bussines Goup | | √ | |
| 34 | Pacific industry (promise water) | √ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 35 | Unique water | | √ | |
| 36 | Sebeta agro industry | √ | | |
| 37 | Etete milk processing | | √ | |
| 38 | Loni milk processing | √ | | |
| 39 | Family milk processing | | √ | |
| 40 | Natan milk product | √ | | |
| 41 | Melkam endale milk processing | √ | | |
| 42 | ዞል ክረሜላ ፋብሪካ | | √ | |
| 43 | ስዊት ወርልድ ኮንስትራክሽን | √ | | |
| 44 | ሄለን ሀሰን | √ | | |
| 45 | ሐላዋ ክረሜላ | √ | | |
| 46 | ጃሰም ትሬዲንግ | | √ | |
| 47 | ሂባ ክረሜላ ኃ/የተ/የግ/ማ | √ | | |
| 48 | ባለልታምር ክረሜላዎች | | √ | |
| 49 | ቢራቢሮ ጣፋጭ ክረሜላ አምራች ድርጅት | | √ | |
| 50 | ኢታ ፊት የምግብ አምራች | | √ | |

**ማስገንዘቢያ፡** ለኦዲቱ 50 ፋይሎች እንዲቀርቡ ተጠይቀው የቀረቡት 27 ብቻ ሲሆኑ ቀሪዎቹ 23 ፋይሎች ለኦዲት አልቀረቡም

## አባሪ 6፡ በድርጅቶች ሊሟሉ የሚገባቸው ሁኔታዎች ዝርዝር

| መሟላት የሚገባቸው ነገሮች | የድርጅቶች ስም ዝርዝር | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ገትስ አግሮ ኢንዱስትሪ | ሲልቫ አልኮልና ለስላሳ መጠጦች | አሃዲክስ ፉድ ኮምፕሌክስ | አፍሪካ ሃላፊነቱ የተ/የግ/ማ | ሆላንድ ዲየሪ | አዲስ ሞጆ የምግብ ዘይት (ሞጆ) | ሼባ ትራ አስመጪ ና ላኪ | አዲስ ሞጆ የምግብ ዘይት (አ.አ) |
| የድንገተኛ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ | × | √ | √ | √ | √ | √ | × | √ |
| የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ | × | √ | × | √ | × | √ | × | √ |
| ፍሳሽ ማስወገጃ | × | √ | √ | √ | × | √ | × | × |
| የአየር ሙቀት ማስተካከያ(AC) | √ | √ | √ | √ | × | × | × | √ |
| የላውንደሪ አገልግሎት | × | × | × | × | × | × | × | × |
| የአደጋ ጊዜ መውጫ በር | × | × | √ | × | × | √ | × | × |
| ስቴሬላይዘር (sterilizers) መሳሪያዎች | × | × | | | × | × | | × |
| ማቀዝቀዣ የተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎች | | × | × | | × | × | | × |

**<u>መግለጫ</u>**

√ **አለ** ×**የለም**

## አባሪ 7፡ በባለስልጣን ሬድ ኢንስፔክትድ ናቸው ተብለው በ 2010 እቅድ ተይዘው የነበሩ የተዘጉና አድራሻቸው የማይታወቅ ድርጅቶች

| ተ.ቁ | የድርጅቱ ስም |
|---|---|
| | ሬድ ኢንስፔክትድ ውስጥ ገብተው ነገር ግን የተዘጉና አድራሻቸው የማይታወቅ ድርጅቶች |
| 1 | ገንደ ሮባ INC. |
| 2 | ፉአድ አሊ አብዱላሂ የምግብ ውጤቶች አስመጪ |
| | **የውጭ ማስታወቂያ የሌላቸውና አድራሻቸው የማይታወቅ** |
| 3 | ላኪ ኢንዱስ |
| 4 | ኤም. ኃላፊነቱ የተወሰነ የአሞሌ ጨው ማምረቻ ኢንተርፕራይዝ |
| 5 | ሽዛዝ የዘይትና ጣፋጭ ምግብ |
| 6 | ሀሰን ቂጣታ |
| 7 | ይመር አሊ የምግብ ጨው አከፋፋይ |
| 8 | ፋይሰል አብዲ የምግብ ውጤቶች አስመጪ |
| 9 | ሽዛዝ የዘይትና ጣፋጭ ምግብ |
| 10 | ዱከም ሰካ ቢዝነስ ግሩፕ ማቀነባበሪያ |
| | **አድራሻቸው ታውቆ የውጭ ማስታወቂያ የሌላቸው** |
| 11 | ሆላንድ ዴየሪ |
| 12 | አሀዱክስ የምግብ ማምረቻ |
| 13 | ኢስት አፍሪካ ታይገር ብራንድስ ኢንዱስትሪ |
| 14 | ጀነሲስ ፋርም |
| 15 | አፍሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 16 | አዲስ ሞጆ የምግብ አይት ኮምፕሌክስ |

አባሪ 8

ፈቃድ ሳያወጡ ምግብ የሚያመርቱና የምግብ ጥራት ቁጥጥር (የላብራቶሪ ሥራ ) የሚሠሩ ድርጅቶች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የድርጅቱ ስም |
|---|---|
| 1 | ኤልፎራ |
| 2 | ጀነሲስ |
| 3 | ኤርሞን የገበታ ጨው |
| 4 | አባይ የገበታ ጨው |
| 5 | ቡስኪ የገበታ ጨው |
| 6 | ማሂር የገበታ ጨው |
| 7 | ንጹህ የገበታ ጨው |
| 8 | ብሌስ አገሪ ፉድስ ላብራቶሪ |